የማንቂያ ደወል

እስላማዊ አክራሪነትና ኢትዮጵያን እስላማዊ ሃገር ለማድረግ እየተሰራ ያለ ሥራ

Islamic Radicalism and the Process of Islmaizing Today's Ethiopia

በያገባኛል በዕምነት
የመጀመሪያ እትም ሐምሌ 2004

ከእንቅልፍ የምትነሱበት ሰዓት አሁን እንደ ደረሰ ዘመኑን እወቁ...
ሮሜ 3:11

ምሥጋና

ሽክፅውን በልቤ አስቀምጦ ወደ ቋሚ ማስታወሻ እንድቀይር አስጀምሮ ላስፈፀመኝ እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይሁን::

- ይህቺ አነስተኛ ማስታወሻ እውን እንድትሆን በሀሣብ መረጃ በመስጠት እና በገንዘብ ለደገፉኝ ሁሉ የከበረ ምስጋናዬ ይድረሳቸው::
- የእጅ ፅሑፌን ሳይሰለቹ ወደ ኮምፕዩተር ፅሑፍ የቀየሩልኝን ወገኖች ሁሉ እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርካቸው
- በመጨረሻ ውሑፉን አንብበው ሰነ ጽሑፋዊና ሕጋዊ መልክ ያሲያዙትን ወገኖች ሁሉ አመሰግናለሁ::

መታሰቢያነቷ

የወንጌል ብርሃን እንዳይጠፋ ሲደክሙ
ሕይወታቸውን ሳጡ ወገኖቻችን ሁሉ::

መብቱ መሕግ የተጠበቀ ነው 2004
All Rights Reserved

ስለ ፅሑፉ አስተያየት ለመስጠት ለምትፈልጉ ወይም ተጨማሪ መረጃ ያላችሁ በሚከተለው አድራሻ ሀሣባችሁን ልታደርሱን ትችላላችሁ::

ስልክ 09 10 88 78 87

09 31 30 40 44

ማውጫ ገፅ

1. መግቢያ ---------- 1
2. ኢትዮጵያን እስላም የማድረግ ሂደት እጀማመር ---------- 8
   2.1 የግራኝ አህመድ ወረራ ---------- 10
   2.2 የሱዳን መሐዲዎች ---------- 11
   2.3 የጣልያን ወረራ ---------- 12
   2.4 የዚያድ ባሬ ወረራ ---------- 13
3. ወሀቢያና ወሀቢያ ፍልስፍና መቼና እንዴት ተጀመረ ------ 14
4. ወሀቢያ ኢትዮጵያ ውስጥ ለማደግ የተጠቀመባቸው ስልቶች ---------- 19

ሀ/ ሐይማኖታዊ

4.1 ሥራውን የማደራጀትና የመምራት ስልት---------- 19
4.2 የሕትመትና የሥርጭት ስልት ---------- 20
4.3 የካሴት አገልግሎት ስልት ---------- 27
4.4 የመስጊድ ግንባታ ስልት---------- 28
4.5 የመደበኛ ቋንቋ ትምህርት የማስፋፋት ስልት--------- 28
4.6 የአረቢኛ ቋንቋን የማስፋፋት ስልት ---------- 31
4.7 ቤ/ክንን የመርገም ስልት ---------- 32
4.8 የጉሣ መሪዎችን አስቀድሞ በመያዝ የማስለም ስልት ---------- 33
4.9 መ/ቅዱስን በተሳሳተ መንገድ የማስጠናት ስልት ---- 33
4.10 ገጠሩን ትኩረት አድርጐ የመንቀሳቀስ ስልት ------- 34
4.11 የንግድ ቦታዎችን በማለሰብ ስም መመራትና በሊዝ በመግዛት ለመስጂድ መስሪያነት ማዋል ---------- 34
4.12 ለዘብተኛውንና ባሕላዊውን እስላም አክራሪ የማድረግ ስልት----------35

ለ/ፕሮፓጋንዳ ፖለቲካዊ አካሄድ ስልት

4.13ታሪክን የማዛባት (የማስለም) ስልት---------- 35
4.14እስታቲስቲካዊ መረጃ የማዛባት ስልት---------- 42
4.15የመንግሥት ሥልጣን የመያዝ ስልት---------- 47

ሐ/ ኃይል የመጠቀምና ትንኮሳ

4.16 ትንኮሳና ጥቃት የመፈፀም ስልት---------- 51
4.17የቴኪንዶና የማርሻል አርት ሥልጠና---------- 52
4.18መ/ቅዱስንና የክርስትና እምነትን በሀትመትና በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ማጥላላት---------- 53
4.19የክርስቲያኖችን ኃይል የመበታተን ስልት---------- 54
4.20የጦር መሣሪያዎችን የማደራጀት ስልት---------- 55
4.21ከክርስቲያች ጋር ግንኙነት ማድረግን ማቋረጥ-------- 55
4.22 የእስላምና ታሪክ የመድገም---------- 55
4.23ሽብር የመንዛት ጅሀድ በማወጅ ጦርነት የመክፈት--- 56
4.24ቦታዎችን የመቆጣጠር ስልት ---------- 58
4.25መረጃ ሰጭዎችን ሚስጥራዊ ቤቶች የመጠቀም ስልት---------- 59
4.26በቴሌቭዥንና በሬድዮ ክርስትናን የማጥላላት ዘዴ -- 59
4.27በክርስቲያኖች ተጨቁነናል የሚል ጩኸት ማሰማት---------- 59

መ/ሥነ ልቦናዊ ሥልት

4.28ከተሞችን መውረር (ማፈናቀል)---------- 60
4.29መረጃዎችን የራስ ማድረግ---------- 61

ሠ/ በኢኮኖሚ የማጠናከር ስልት

4.30ተከታዮቻቸውን በኢኮኖሚ የበላይነቱን እዲወስዱ ማድረግ ---------- 61

ከእንቅልፍ የምትነሱበት ሰዓት አሁን እንደ ደረሰ ዘመኑን እወቁ... ሮሜ 13 ÷ 11

ረ/ የኢንቨስትመንት የንግድ ሽርክናና ዲፕሎማሲያዊ መስክ
4.31ኢንቨስትመንትን የንግድ ሽርክናና ዲፕሎማሲያዊ መልክን
የመጠቀም ስልት---------- 63

ሰ/ ሌሎች ልዩ ልዩ ስልቶች
4.32የቁጥር እድገት የመጨመር ስልት---------- 65
4.33ኢትዮጵያውያን ሴቶችን ወደ ዐረብ ሀገራት የማፍለስ
ስልት---------- 66
ክፍል ሁለት
5.ኢትዮጵያን ኢስላማዊ የማድረግ ሂደት ጀርባ ያሉት እነማን
ናቸው?-- 68
ክፍል ሶስት
የአብያተ ክርስቲያናት(የክርስቲያኖች) ሚና ምን መሆን
አለበት?---------- 74
ማጠቃለያ---------- 80

ከእንቅልፍ የምትነሱበት ሰዓት አሁን እንደ ደረሰ ዘመኑን እወቁ... ሮሜ 13 ÷ 11

መቅድም

ደወል የሚያስፈልገው አንድም የዘነጋን ሰው ለማስታወስ ሲሆን አንድም ደግሞ ያንቀላፋን ሰው ለመቀስቀስ ነው ይህቺ አነስተኛ ፅሑፍ የማንቂያ ደወል የሚል ስያሜ የተሰጣትም የኢትዮጵያን ክርስቲያኖች መሪዎችንና አገልጋዮችን ለማስታወስና ለመቀስቀስ በማሰብ ነው ይህን ለማለት ምክንያት የሆነኝ ነገር ካለፉት ስምንት ዓመታት ጀምሮ የዚህን ሐይማኖት ምንነት ባሕሪውንና ዓለም አቀፍ እንቅስቃሴ እንዳጠናና እንድከታተል እግዚአብሔር በልቤ ውስጥ ትልቅ ሸክም ካስቀመጠ በኋላ እውነትም እኛ አፍሪካውያን ክርስቲያኖች በትልቅ እንቅልፍ (መዘናጋት) ላይ እንዳለን ለመገንዘብ ችያለሁ

በዓለም ላይ በአሁኑ ወቅት እዚህም እዚያም ትላልቅ ሐይማኖታዊ ግጭቶች ተነስተው ትላልቅ ጥፋቶች ደርሰው በዜና ማሰራጪያዎች በየዕለቱ ስንሰማ ከዜናነቱ ባለፈ ለምን? እንዴት? ብለን አንጠይቅም በሐይማኖታዊ ስርዓቶቻችን ታጅበን በዙሪያችን የሚፈፀሙ ጉዳዮች እኛን እንደማይመለከቱን በማሰብ ውስጥ እንድንቆይ በማድረግ ጠላት በጣም አታሎናል ሩቅ እንዳለ አድርገን የምናስበው አክራሪ እስልምና ዓለምን ሁሉ አክራሪ የማድረግ አስተሳሰቡ በዙሪያችን ባሉት እነ ኬኒያን በመሳሰሉ ሀገሮች በተደጋጋሚ ጥቃት ሲፈፅሙባቸው ቆይቶ ላለፉት አምስት እና ስድስት ዓመታት ግን ወደ እኛም ሀገር ገብቷል እንደ እኛ እንቅልፍ ላይ የነበረችው ናይጀሪያ በአሁኑ ወቅት ፈተና ውስጥ ትገኛለች።

በሺህ የሚቆጠሩ ክርስቲያን ልጆቿ በቤተክርስቲያን ውስጥ በተጠመዱ ፈንጂዎች ሕይወታቸው አልፏል አልፎ አልፎ እንደምንሰማው ከሆነ ክርስቲያኖቹ የኃይል እርምጃ እስከ መውሰድ ደርሰዋል

ወደ ሀገራችን ሁኔታ ስንመለስ ደግሞ ከነዚህ ተደጋጋሚ ትንኮሳዎች አልፎ እዚህም እዚያም ጥቃቶችና ግጭቶ ከተፈፀሙ በኋላ ሐይማኖታዊ መቻቻልን ለማምጣት መንግሥትና ሕብረተሰቡ በመቻቻል ዙሪያ ተከታታይ የውይይት መድረኮችን አዘጋጅተው በማግባባትና የእርቅ ስራ ሲሰሩ አይተናል ሰምተናል ሐይማኖታዊ መቻቻልን ለማምጣት የሚረዱ ተቋማትም በይፋ ተቋቁመው እየሰሩ ይገኛሉ የነዚህ ተደጋጋሚ ውይይቶች መካሄድና በሐይማኖት መቻቻል ላይ የማሰሩ ተቋማት መበራከት ከፊት ለፊት አደጋ እየመጣ እንዳለ የሚያሳዩ ጠቋሚ ምልክቶች (Indicators) መሆናቸውን ልብ ልንል ይገባል በልሆችና ጥበበኞች መሪዎችም መሆን የሚያስፈልገንም ለዚህ ነው ዘመኑን መመርመርና መዋጀት የሚያስፈልገው አሁን ነው

ይህን ስንል እስልምና በሰላማዊ መንገድ አይስበክ ማለታችን አይደለም ሐይማኖታቸውን በሰላማዊ መንገድ ማስተማር መብታቸው ነው መብታቸው የማይሆነው የሀገርና የሕዝብን ሰላም በማናጋት አይሁን ነው እያልን ያለነው

ይህቺ አነስተኛ ዕሑፍ በእጃችሁ እንድትገባ የተደረገችው በትክክለኛው ጊዜ እንደሆነ ይሰማኛል ምክንያቱም ነገሩ አድጐና ልንቆጣጠራቸው የማንችላቸው ሁኔታዎች ተፈጥረው በኖርዌ አገር እንደተፈፀመው የጅምላ ጭፍጨፋ ዓይነትና ዛሬ የሰሜን ናይጀሪያ ክርስቲያኖች የሚወስዱትን የስጋ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ከመፈጠራቸው በፊት እንድንነቃ ጥሪ የምታደርግ በመሆኗ ነው

አክራሪው እስልምና የትኛውንም የማግባቢያ ቋንቋ ቢጠቀምና በለሰለሰ አንደበት ሊነግረን ቢሞክር ልንቀበለው አንችልም ናይጀሪያውያንን ያታለሏቸው በነዚሁ በለሰለሱ አንደበቶች ተጠቅሞ ነው እስላም ማለት ሰላም ማለት ነው በሐይማኖት ማስገደድ የለም ወዘተ የሚሉት ሁሉ ሽንገላዎች ናቸው ጳውሎስ ሀሣቡን አንስተውምና ብሏል

- እቅዳቸው አፍሪካን በመቶ አመት እስላም ማድረግ ነው
- የኢትዮጵያን ክርስትና በውድም ይሁን በግድ ማፍረስ ነው
- ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በነሱ አገላለፅ እስልምና በኢትዮጵያ ከመታገስ ወደ መታገል ተሸጋግሯል
- በመጨረሻም በኢትጵያ ውስጥ እስላማዊ መንግሥት በማምጣት ክርስትናን ከኢትዮጵያ ምድር መለረዝ ዋና ዓላማቸው ነው

ስለዚህ ወገኖቼ ሆይ ከእንቅልፍ የምንነሳበት ወቅት ላይ መድረሳችንን ጊዜው ያመለክታል ምልክቶችም እየተናገሩ ናቸውና እንንቃ እግዚአብሔር አምላክ በልቤ ያስቀመጠውንና እረፍት የሚነሳውን ሸክም ባለፉት አምስት አመታት በየጉባኤዎቹ ተገኝቼ ሳካፍል ቆይቻለሁ ሆኖም በዚህ ልረካ ባለመቻሌ በሁላችንም ላይ ምስክር ሆና እንድትቆም ይህቺን አነስተኛ ማስታወሻ በእጃችሁ ላይ በማኖር ዘመንን እንድትመረምሩና እንድትዋጁ የማንቃት ኃላፊነቴን የተወጣሁ እንደሆነ እራሴን እቆጥራለሁ።

የሰጠኝን ሸክም በዚህች አነስተኛ የፅሑፍ ማስታወሻ ለማስፈር አስጀምሮ ያስጨረሰኝን እግዚአብሔር አምላኬን አመሰግናለሁ።

መግቢያ

በ1ኛ ዜና 12:32 ላይ ‹‹ዘመኑን የተረዱና እስራኤላውያንም ምን ማድረግ እንደሚገባቸው የተገነዘቡ የይሳኮር ልጆች ሁለት መቶ አለቆች ... ›› የሚል የእግዚአብሔር ቃል ክፍል እናገኛለን፡፡ ይህ የእግዚአብሔር ቃል ክፍል የሚናገረው ስለመሪዎች ኃላፊነትና ተግባር ሲሆን ከህዝብ ፊት የቆሙ መሪዎች ዘመኑን አንብበውና ተረድተው ተከታዮቻቸው ማድረግ ያለባቸውን በመንገር ህዝብን ማዘጋጀት እንዳለባቸው ያስገነዝባል፡፡ ይህ ዘመንን የማየትና የመረዳት መርህ በአዲስ ኪዳንም በትዕዛዝ መልክ የተላለፈበትን የኤፌ. 5:16 እና በወቀሳ ወይም በዘለፋ መልክ የተቀመጠውን የሉቃ. 12:56 ሐሳብ ያስታውሰናል፡፡

ወንጌል በባህሪው ተቃውሞን፣ ስደትን፣ እንግልትና ሞትን የሚያስከትል መሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ቢሆንም እነዚህ ነገሮች ሁሉ እንዳሉ ሆነው አማኞች በተቃውሞ፣ በስደትና በሞት ውስጥ የወንጌል አሳት እንዳይጠፋ መጋደል እንዳለባቸው የእግዚአብሔር ቃል ያስተምረናል፡፡ በተለይ መሪዎች በዚህ ረገድ ኃላፊነታቸው እጥፍ ድርብ ነው፡፡ እነዚህ የወንጌል ተግዳሮቶች የሚከሰቱት በዘመን ውስጥ እንደ መሆኑ ዘመንን የማየትና የመረዳት አስፈላጊነት ብሎም አማኞችን የማዘጋጀት ኃላፊነት ከላይ በጠቀስናቸው የእግዚአብሔር ቃል ክፍሎች ላይ ስንመለከት የመሪዎችን ድርሻ ከፍተኛነትን እንረዳለን፡፡

እንደኔ መረዳት ዛሬ ክርስትና በዓለም ላይ ሁለት ዋና ዋና ተግዳሮቶች ከፊቱ ቆመው እንዳይንቀሳቀስ እያደረጉት እንዳለ እገነዘባለሁ፡፡

የመጀመሪያው የድህረ ዘመናዊነት አመለካከት ውጤት የሆነው ዘመናዊነትና ዓለማዊነት ሲሆን ይህ ፍልስፍና በአብዛኛው ክርስትያን ዘንድ ሥፍራ ያገኘበት ወቅት ላይ እንገኛለን፡፡ “ቋሚ የሆነ የስነ ምግባረ ህግ የለም”፣ የሚጠቅምህን አንተው ውስን ራስህን፣ ውደድ፣ ዋናው ጉዳይ ራስህን ማስደሰት ነው፣ ትክክልና ትክክል ያልሆነ (Right & Wrong) የሚባል ነገር የለም፡፡ ትክክል ወይም እውነት አንፃራዊ ነው፡፡›› ወዘተ. የሚሉ አስተሳሰቦች በክርስትና ዘንድ ሥፍራ ባገኙበት ወቅት የብዙዎች ህይወት እያሽቆለቆለ ስላለ ቤተ ክርስቲያን በታላቅ አደጋ ላይ ትገኛለች፡፡ ማንም ከማንም ባልተሻለ ሁኔታ በኢሳ.1:6 ላይ እንደተቀመጠው “ሰው ሁሉ ከራስ ፀጉር እስከ እግር ጥፍር ድረስ ታምሞአል፡፡” የእውነተኛው ክርስትና እሴቶች በዘመናዊነት ስም እየወደሙ ናቸው፡፡ ከቅድስና ይልቅ እርኩሰት፣ ሴሰኝነትና፣ ዘማዊነት፣ ተስፋፍቶ በቅድስና ለመኖር የሚሞክሩት እየተወገዙና ሌሎች ደግሞ በአንባሩ እየተሞገሱ ያሉበት፣ የክርስትናን እሴት ጠብቀው ለመኖር የሚፈልጉት ከመድረክና ከቤተ ክርስቲያን ተገፍተው የወጡበት በአንባሩ ዘመኖቹ መድረኮችን የወረሩበት ይህች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ተግዳሮት ገጥሟት መንታ መንገድ ላይ የቆመች የምትመስልበት ወቅት ላይ እንገኛለን፡፡ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሺህዎችና ሚሊዮኖች ክርስቲያኖች

ያሉባት እንጂ ብዙዎች ደቀመዝሙርት ያልሆኑባት ሆና እናገኛታለን።

ሁለተኛው ተግዳሮት ደግሞ የፖለቲካዊ እስልምና በዚህች አገር ሳይታወቅ ሥር መስደዱና አደገኛ ደረጃ ላይ መድረሱ ነው። ዓለም አቀፉ ፖለቲካዊ እስልምና በባህሪው ከእኛ ሌላ ሃይማኖት አይኖርም እሺ ያለውን በውድ እምቢ ያለውንም ደግሞ በኃይል አስልማለሁ በሚል ፍልስፍና የሚንቀሳቀስ የዓለም የሽብርተኝነት ማዕከል ሆኖ የሚሠራ ኃይል ነው። ባለፉት 10 እና 15 ዓመታት ውስጥ ውስጡን ሲደራጅ ቆይቶ ይፋ አንቅስቃሴውን በጅማ፣ በባሌ፣ በሐረር፣ በአርሲና በወሎ ክርስቲያኖች ላይ ጀሀድ ያወጀውን ጅሀዳዊ አክራሪ እስልምና (ወሀቢያ) ወይም ሰለፊያ በመባል የሚታወቀው የእስልምና ክንፍ በሀገር ቤት ውስጥ በአወሊያ ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ሲሰራበት የነበረው መዋቅር እንዲፈርስ ሲደረግ ከጥር ወር 2004 ዓ.ም መጀመሪያ እስከ የካቲት ውር 2004 ዓ.ም ድረስ ፀረ-ሃይማኖታዊ እስልምናና (ባህላዊ እስልምና) ፀረ-መንግስት አቋም በማራመድ ሀገሪቱን ወደነውጥ ውስጥ ለማስገባት በአደሲ አበባና በክልሎች መጠነ ሰፊ ንቅናቄ በመፍጠር ላይ የሚገኝበት ሁኔታ እንዳለ ይታወቃል። ይህ ንቅናቄ በውጪ ሃይሎች የተደገፈ እንደነበር መንግስት ካወጣቸው መግለጫዎች ማወቅ ተችሎአል። ይህ የነውጥ ንቅናቄ በፍጥነትና በትእግስት በቁጥጥር ስር ባይውል ኖሮ ለሃገሪቱ ሰላምም ሆነ ለክርስትና እምነት እጅግ አደገኛ ይሆን ነበር። እግዚአብሔር ግን መንግስትን ተጠቅሞ እንቅስቃሴውን ተቆጣጠረወ።የሚገርመው ግን ብዙ ክርስቲኖች በተለይም ብዚዎች

ዋና ዋና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህ እንቅስቃሴ እየተካሄደ እንዳለ እንኳን አለማወቃቸው ነው። ነገሮች ከቁጥጥር ውጪ ወጥተው ችግር ወደእያንዳንዱ አማኝ ቤት ሲደርስ መሪዎች ከህዝቡ እኩል ቢነቁ ምንም ፋይዳ ስለማይኖረው ይህንን ሁለተኛውን ተግዳሮት ምን ደረጃ ላይ እንዳለና የሚጠቀምባቸውን ስልቶች ማወቁ እጅግ አስፈላጊና ከመሪ ተግባሮች አንዱ ሲሆን ስለሚያስፈልግ በጽሁፍ መልክ ቀርቦ መሪዎች እንዲያገኙት ማድረግ መርጠናል።

የፖለቲካዊ እስልምና (አክራሪ እስላም) ወቅታዊ ግብ "ወደፊት ዓለም በሙሉ እስላም ትሆናለች በዚያን ጊዜ ከቀሬሽ ጎሳ ማለት ከነቢዩ መሐመድ የዘር ሐረግ ዓለምን የሚገዛ አንድ መሪ ይነሳል" .የሚል እምነት አለው። በዚህ አቅድ መነሻነት የአፍሪካ ህዝብ በድህነት የተያዘ በመሆኑ አረቦችና ከነዳጅ የሚገኘውን ከፍተኛ ገቢ ለሃይማኖቱ ማስፋፊያ ስለሚያውሉት አፍሪካን በመቶ ዓመት ሙሉ በሙሉ እስላም ለማድረግ በከፍተኛ ሁኔታ እየተንቀሳቃሱ ይገኛሉ። ከአፍሪካ ከተመረጡ ጥቂት ሀገሮች ኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ መሆኗን ሪን ሀርድ ኔልስ "እንድረስላቸው በሚለው መጽሐፋቸው ገጽ 11-12 ላይ መግለፃቸውን መጋቢ ዲሰን መንዲድ ጽፈዋል።

የመጀመሪያው ተግዳሮት በዚህ መልክ ክርስትናን ባዳከመበት ሁኔታ ሁለተኛው ተግዳሮት ደግሞ በከፍተኛ የገንዘብ አቅም ተጠናክሮ ሌት ተቀን በሚሰራበት ክርስትናን ተክቶ እስልምናን የሀገሪቱ አፊሴላዊ ሃይማኖት ለማድረግ ጅሀዳዊ እንቅስቃሴ እያካሄደ ባለበት ወቅት ከትላንት ታሪክ ተምረን ህዝቡን ምን ማድረግ እንዳለበት ካላሳየነውና ካላዘጋጀነው ታሳላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶች

ያገለገሉባቸው የሰሜን አፍሪካ ሀገሮች የፈጸሙትን ስህተት እኛም በ21ኛው ክፍለዘመን እንዳንደግመው ያስፈልጋል። ለምሳሌ፦

- ቱኒዚያ፦ (ካርቴጅ) በስደት ምክንያት አንገቱን ተቆርጦ የሞተው ጳጳስ ሲጵሪያኑስ የተወለደበትና ያገለገለበት የክርርስቲያን ሃገር የነበረች
- ሊቢያ፦ "የኢየሱስ" ብቻ (Only Jesus) ጀማሪ አርዮስን ለመምከር ሊቃነ ጳጳሳት የተሰበሰቡበት የክርስቲያን ሀገር የነበረች
- ግብጽ የነማርቆስ ሐዋሪያዊ አገልግሎት የተጠናከረበትና የእስክንድሪያው ክሊምናተስ (Clementus) እና እነ አርጊነስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ያስተማሩበት ሀገር ዛሬ የእስልምና ሃይማኖት የነገሠባቸውን ሁኔታ ማሰብ ተገቢ ይሆናል እነ ጳውሎስ የተከሉአቸው የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያንን ስናይ የቀድሞው ቆስጥንጥኒያ (Constantinople) የዛሬዋ ኢስታንቡል ዕጣ ፈንታ እኛን ላይገጥመን ምን ዋስትና ይኖረናል?

ዛሬ በእስልምና አክራሪዎች ምክንያት አሁን ያለው ሰላማዊ ሁኔታ ቢደፈርስ ወንጌልን የማድረሱ እድል ባይቆም ቢያንስ እንደሚዘገይ ማየት ይችግራልን?

በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ወትሮውንም በራሳችን ጉዳይ ተይዘን ለጥቅም፤ ለክብርና ለዝና ሲባል መድረክ በማሟሟቅ ላይ ስለተጠመድን የወንጌል ሥራ እየተረሳ

ባለበት ሁኔታ ስደት ቢጀምር በሀገራችን ያለው የወንጌል ሥራ እንዴት ሊቀጥል ይችል ይሆን?

ዛሬ በምዕራቡ ዓለም በምቾትና በቅንጦት ምክንያት የክርስትና ዕምነት ለህይወት ጥያቄ መልስ መስጠት እንደሚይችል ተቆጥሮ አዲሱ ትውልድ ፍፁም ዓለማዊ በሆነበትና ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አዛውንቶች ብቻ የቀሩበትን ሁኔታ ስናይ በአውሮፓ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት ሳይቀሩ ግብረ ሰዶማውያን እየሆኑ መምጣት ቤተ ክርስቲያን ለመስጊድና ለፊልም ቤቶች እየተሸጡና በአሁኑ ወቅት አውሮፓ በእስልምና እየተወረረ መምጣቱን ስንሰማ እኛ ጋ የማይደርስ መስሎን ተዘናግተናል ከገባን ደግሞ ይህ ለኛ ብርቱ ማስጠንቀቂያ ነው።

ሰሞኑን በሚያዝያ ወር 2004 ዓ.ም መጀመሪያ ከቴሌቪዥን ጣቢያ በተላለፈው ዜና የሰማነው በኖርዌይ የ77 ሰዎች መገደል ምክንያት ሌላ ሳይሆን አንድ ለክርስትና የቀና ሰው የወሰደው ሥጋዊ እርምጃ ነው። ይህ ሰው ፍ/ቤት ቀርቦ በሰጠው ቃል ሀገሬ በእስላም ተወራ ላለማየት የወሰድኩት እርምጃ ነው በማለት አፍ አውጥቶ ተናግሯል።

እንግዲህ ከዚህ ድርጊት የምንረዳው በወቅቱ መሠራት ያለበት ሥራ ሳይሰራ ስለቀረ በረፈደ ጊዜ የተወሰደ ፋይዳ ቢስና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ውጤት የሌለው የተሰፋ መቁረጥ እርምጃ ነው።

የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማም "ቀን ሳለ የላከኝን ሥራ ላደርግ ይገባኛል።" ዮሐ. 9፡4 የሚለውን የጌታ ቃል እውነት ለማስታወስና ወንጌላውያን አማኝ መሪዎች ቆም ብለው እንዲመክሩ ለማስታወስ ነው። ይህ ሳይሆን ቀርቶ ከረፈደ በኋላ በሚደርስ ችግር ማዘን፣ መፀፀት እና ቁጭት ፋይዳ ቢስ ስለሆነ ዘመኑን አይቶ መፍትሔ ማበጀት የጥበበኛ መሪ ተግባር ነው።

ናይጄሪያ በወቅቱ ማድረግ ያለባትን ባለማድርጓ እነሆ በአሁኑ ሰዓት ችግሩን ፊት ለፊት እየተጋፈጠችው ትገኛለች በአሁኑ ወቅት ቦኮሀራም የተባለ ፅንፈኛ ቡድን ብዙ ክርስቲያኖችን እየገደለና ቤተክርስቲያናትን በፈንጂ እያጋየ ይገኛል የሀገሪቱ መንግሥትም ጉይዩ ከቁጥጥር ውጪ እየሆነበት ስለመጣ ሰኔ 11 ቀን 2004 ዓ.ም በሰሜኑ የናይጄሪያ ግዛት ሰዓት አላፊ አውጀአል። እኛስ ከናይጄሪያ የምንማረው ምን አለን? ቶሎ ብለን ማድረግ ያለብንን ነገር ካላደረግን ዋጋ የምንከፍልበት ወቅት ላይ ደርሰናል።

ክፍል አንድ

I. ኢትዮጵያን እስላም የማድረግ ሂደት አጀማመር

በታሪክ እንደሚታወቀው እስልምና በዐረብ ምድር ተፈጥሮ የመጀመሪያዎቹ አማኞች በእምነታቸው ምክንያት በተሰደዱበትና ስደተኞቹም የኢትዮጵያን ምድር ከረገጡበት ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ ከመካ ቀጥሎ እስልምናን የተቀበለች ሁለተኛ ሀገር ናት በማለት ያስተጋባሉ። ለዚህ እምነታቸው እንደ ማስረጃ አድርገው የሚያቀርቡት ደግሞ በ620 ዓ.ም (እስልምና በተመሠረተ በ50 ዓመት እድሜው ላይ መሆኑ ነው።) በጊዜው ኢትዮጵያን ያስተዳድር የነበረው ንጉስ ነጃሺ እስልምናን ተቀብሏል በማለት የፈጠራ ታሪክ ጽፈው እሱን እየተቀባበሉ በማስተጋባት ላይ ይገኛሉ። ታሪኩን ለአንባቢዎች ፍርድ በመተው ተፈፀመ የተባለውን የእስልምና እምነት መቀበል ጉዳይ በዚህ መልክ ማቅረብ የተሻለ ይሆናል። በ620 ዓ.ም (እስልምና በአግሩ ቆሞ በአካባቢው እንኳ መድረስ ባልቻለበት ወቅት) በዓለም ታላቅና ገናና ለነበሩት ነገስታት እስልምናን እንዲቀበሉ የዛቻ ደብዳቤ ጽፎላቸው እንደነበረና ዛቻውን በመፍራት እስልምናን ተቀብለዋል ከተባሉት አገሮች መካከል ኢትዮጵያዊው ንጉስ ይገኝበታል ይላሉ። በጊዜው ኃያላን ሆነው ብዙ አገሮችን ያስተዳድሩ የነበሩ ነገሥታት ውጊያ አድርገው ሳይሸንፉ እንዴት 50 ዓመት እድሜ ባለው አዲስ እምነት መሪ ዛቻ ተሸንፈው እስልምናን እንደተቀበሉ ለማመን ይቸግራል። ከዚህ በተጨማሪ የእርሱን ተከታዮች እንዲያስጠጋለት መጠጊያ የሚፈልግ አካል እንዴት ዛቻውንስ ይፈራል?

ሌላው የታሪኩን እውነተኛነት ጥያቄ ውስጥ የሚከተው ደግሞ በኢትዮጵያ የነገሥታት ታሪክ ውስጥ በዚያን ጊዜም ሆነ ከዚያ በኋላ ያስተዳደሩት ዝርዝር ውስጥ ነጃሺ የሚል ንጉሥ አለመነሳቱ ነው። ደግሞም በታሪክ እንደሚታወቀው ነገሥታት ሲሞቱ ንግሥናውን የሚቀበለው አልጋ ወራሽ ይሰልም ነበር። የጥንታዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በ1991 ዓ.ም የፈጠራ ታሪኩን በይፋ አውግዛ መግለጫ አውጥታለች። አንዳንድ የዐረብ ፀሐፊዎችም ይህንን የፈጠራ ታሪክ ከሌሎች የዓለም ታሪክ ተነስተው ባሰራጩት ጽሑፍ የፈጠራ ታሪክ መሆኑን አረጋግጠዋል። በኢትዮጵያ ታሪክ ተመዝግቦ የተገኘው የወቅቱ ገዥ ንጉሥ አርማህ ወይም ንጉሥ አድርአዝ ነው እንጂ ነጃሺ የሚባል አልነበረም። በአርኪዮሎጂ ጥናትም እንደተረጋገጠው ንጉሡ የሚጠቀምባቸው ገንዘቦች ላይ በሙሉ የመስቀል ምስል ነው የሚታየው እንጂ የጨረቃ አልነበረም።

ዛሬ ዐረቦች የእኛዎቹን ጨምሮ በጽሑፎቻቸው ኢትዮጵያ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የእስላም ሀገር ነበረች አሁንም ነች እያሉ ይከራከራሉ። በዚህ ሀሳብ መነሻነት ኢትዮጵያ የክርስቲያን ሀገር መሆኗ ቀርቶ የእስላም ሀገር ናት ብለው ስለሚያምኑ ከእንግዲህ ወዲህ ሙሉ በሙሉ እስላም መሆን አለባት። በምሥራቅ አፍሪካ ካሉት ሀገሮች ሁሉ ጠንካራው የኢትዮጵያ ክርስትና በስላምም ይሁን በጂሃድ ፈርሶ እስላማዊ መንግስት መመሥረት አለበት የሚል ዕኑ አቋም አላቸው። በተለይ ነጃሺ የሚለውን ስም የሙጥኝ ያሉበት ምክንያት የዐረብ ባህረ ሰላጤ አካባቢ ሕዝቦችን ልብ ለመሳብ የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው። (በእርግጥ ኢትዮጵያ ውስጥ መቻቻል አለ እንዴ ከሚል መጽኃፍ የተወሰደ)

ያለፉትን የኢትዮጵያ ታሪክ ስናይ አብዛኛው የጦርነት ታሪክ ሆኖ እናገኘዋለን። የውጪው የጦርነት ታሪኮች አብዛኛዎቹ ወይም

ሁሉም የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጦርነቶች ሳይሆኑ ኢትዮጵያን እስላም የማድረግ ጦርነቶች እንደነበሩ ከጦርነቶቹ ይዘትና ከወራሪዎቹ ማንነት ጋር በማስተያየት የተካሄዱትን ጦርነቶች እንመልከት።

ሀ የግራኝ አሕመድ ወረራ

በትውልድ ሶማሊያዊው ግራኝ አህመድ ኢትዮጵያን እንዲወጋ የተሰጠውን ተልዕኮ ለመፈፀም የሚያስችለውን ዝግጅት ካጠናቀቀ በኋላ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያን የወረረ ሲሆን ይህ ወቅት እስልምናን በማጠናከር አንድ ወጥ የሆነ የእስላም መንግስት የመመሥረት ሀሳብ የተጠናከረበት ወቅት ነበር። ቱርኮች አውሮፓን በመውጋት ላይ ሲሆኑ የግብፅ መምሉክኞ ደግሞ ወደ ቀይ ባህር በመዝለቅ ላይ የነበሩትን ፖርቹጋሎችን ይወጉ ጀመር በየቦታው ጀሃድ ታውጆ ነበር።

ከ1490 እስከ 1540 ዓ.ም ግማሽ ምዕተ ዓመት ለሚሆን ጊዜ በርካታ ሰዎች ከየመን ሂጃዝ ቀይ ባህርን እየተሻገሩ ወደ ዛይል ከዚያም ወደ ሐረርና ደቡብ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ መሥፈር ጀመሩ። ወደ ምስራቅ የተጓዙት ሐረር ላይ ወደ ደቡብ የተጓዙት ደግሞ ባሌ ላይ ከተመሠ። በተለይም ሐረርን የፖለቲካና የሃይማኖት ማዕከል አድርገው አስፋፉት፤ ከዐረቢያ በመጡት የዐረብ ዝርያዎች አማካኝነት መድረሳዎች (የመስጊድ ሃይማኖታዊ ት/ቤቶች) እና መስጊዶች ተስፋፉ።

በ1216 ዓ.ም 143 ዐረቦች ወደ ሐረር መጥተው ከአካባቢው የጦር መሪዎች ጋር በመገናኘት የፖለቲካውን ሥልጣን መያዝ ጀመሩ። ማጎፋዝ የተሰኘ ከዐረቢያ የመጣው ጂሃዲስት ከዐረቢያ የጦርነት ባንዲራና መለከት በማስመጣት ጦርነቱን ቀጠለበት <u>የመካው በረከት</u> 2ኛ ለግራኝ ድጋፍና የጀሃድ ጦርነት ምልክት እንዲሆን ባንዲራ ላከለት። ቱርኮችም ግብፅን ይዘው ወደ ደቡብ የሚያድርጉትን ጉዞ እንዲገታ ያደረገችው ኢትዮጵያ ስለነበረች ቱርክ ለግራኝ አሕመድ ድጋፍ መስጠት ጀመረች። ግራኝም ወደ ሙሉ ጦርነት ለመግባት የሚያስችለውን አስፈላጊ የጦር መሣሪያ ከቱርክ ያገኘ ሲሆን ፈረሶችና አማካሪዎች የተላኩለት ከሳዑዲ ዐረቢያ ነበር። የሳዑዲው ኢማም ደግሞ አንድ መድፍና 200 ጠመንጃዎች ከሁለት መቶ ወታደሮች ጋር ላኩለት። የመን ውስጥ የነበረው የቱርክ ኢማም ደግሞ 10 መድፍና 900 የሰለጠኑ ወታደሮችን ላከለት። በዚህ ዓይነት ዝግጅት ከ1529—1535 ዓ.ም ድረስ ለ7 ዓመታት በተካሄደ ጦርነት ሽዋ፣ አማራና ትግራይ በግራኝ ተያዙ። የአፄ ገላውዴዎስ ዜና መዋዕል እንደሚገለፀው አብያተ ክርስቲያናት ተቃጠሉ፣ ካህናትና ምዕመናን በጭካኔ ታረዱ። የህዝቡ 1/3 ኛው ሲቀር ሌላው በግዴታ ሰለመ። ነገር ግን የካቲት 13 ቀን 1535 ዓ.ም ግራኝ <u>በዙንትራ</u> ሜዳ ተገደለ። በዚህ ጦርነት ክርስቲያን ኢትዮጵያን ለመርዳት ፖርቹጋል በክርስቶፈር ደጋማ የሚመራ 400 የሰለጠኑ ወታደሮችን ልካለች። አፄ ገላውዴዎስ በእነዚህ ተዋጊዎች ምክንያት ከወደቁበት እንዳንሰራሩ ታሪክ ይመሰክራል። በግራኝ አህመድ ጦርነት የቱርክ፣ የሳዑዲ ዓረቢያ እና የየመንን የድጋፍ ሰጪነት ሚና ስናይ ጦርነቱ ወይም የፖለቲካ ወይም የኢኮኖሚ እንዳልነበረ መመልከት ይቻላል።

ለ. <u>የሱዳን መሃዲዎች</u>

እስልምናን በሱዳን በኩል ለማስፋፋት በነበራቸው እምነት አጼ ዮሃንስ <u>"በግድ ክርስቲያን ሁኑ አሉን"</u> በማለት ወደ ሱዳን በተሰደዱ <u>ሙስሊሞች አቤቱታ በ1880 ዓም ጥር 10 ቀን መሃዲዎች በከፈቱት</u>

ጦርነት እስከጎንደር ድረስ በመዝለቅ ቤተክርስቲያናትን በማቃጠል ክርስቲያንን ለማረድ በቅተዋል። በጦርነቱም አጼ ዮሃንስ ህይወታቸው አልፎአል። አፄ ዮሐንስ ሰበብ ሆኑ እንጂ ወትሮውንም ቢሆን ጦርነቱ በእቅድ ውስጥ የነበረ መሆኑን የኢትዮጵያ ታሪክ በሰፊው ዘግቧል።

ሐ. <u>የጣሊያን ወረራ</u>

ከ 1928-1933 ዓ.ም በኢትዮጵያ ላይ የተፈጸመው ወረራ ሁለት ዓይነት ገጽታ ነበረው። የመጀመሪያው ገጽታ አውሮፓ አፍሪካን በቅኝ ግዛት ለመከፋፈል በተወጠነው ውጥን አኩዋያ ሲታይ ወረራው ፖለቲካዊ ይዘት የነበረው ሲሆን ሌላኛው ገጽታው ደግሞ ኢትዮጵያን በጦርነቱ ድል ለማድረግና ከድል ማግስት ለማስተዳደር የተወጠነው ውጥን ግን ሃይማኖታዊ ይዘት ነበረው።

ወቅቱ ሳዑዲ አረቢያና ግብጽ በኢትዮጵያ ውስጥ የመስፋፋት ዘመቻ የተያያዙበት ጊዜ ስለነበረ ጣልያንም ራሱን የእስልምና የበላይ ጠባቂ አድርጎ ያቀረቡበት ጊዜ ነበር። የሳዑዲን ድጋፍ ጠይቆ ወረራው ከሁለት አቅጣጫ ማለትም ከኤርትራና ከሶማሊያ በኩል ስለነበር ለጦርነቱ የሚረዱ ፍቃደኛ ወታደሮች ከአረቢያና ከሌሎች ሃገሮች ተውጣጥተው ተሰጡ። 12 ሺህ ግመሎች ከሳዑዲ ዐረቢያ ተበረከተለት 70000 ወታደሮች የተመለመሉት ከሶማሊያ፤ከሃረር ከደቡብ ኦሮሚያ የእስላም አካባቢዎች ነበር።

ያ ሁሉ ጭፍጨፋና አልቂት የተፈጸመው ክርስትናን ከኢትዮጵያ ገፍትሮ ለመጣል ነበር ሙከራው ዛሬም ድረስ በተለያየ መልኮች ቀጥሎአል ከዚህ ሌላ በዚያ ዘመን የተከናወነውን ድርጊት ትክክለኛ እስላማዊ ተልእኮ አድርገው የሚያምኑበት ሲሆን የተወሰኑት ድርጊቶች በሃረሪ ክልላዊ መንግስት የገንዘብ ድጋፍ በተዘጋጀው <u>አበሻን የማቅናት ዘመቻ መጽሐፍ ላይ ድርጊቱ በደል እንዳይደል</u> በኩራት የሚነገረን ታሪክ ተፅፎልናል።

ጣልያኖችና ሳዑዲዎች ተስማምተው ኢትዮጵያን ሰማስለም የፈጸሙትን ደባ እግዚአብሔር እራሱ ተዋግቶ አሸነፈው። በእነዚያ አምስት የወረራ አመታት እስላሞች ወደ መካ እንዲሄዱ ይበረታቱ ነበር። እነዚህ ወደ መካ እንደሄዱ የሚመለምሉ ተጉዋጉዮች ሞሶሎኒ ለእስላሞች የተሸለ መብት እንደሰጠ የማስረዳት ግዴታ ነበረባቸው። ሳዑዲዎች ደግሞ ወደ መካ ከሚጉዋዙት ኢትዮጵያውያን መስለሞች መካከል ርካሽና የተናቀ ስራን እንዲሰሩላቸው ዜግነት ከመስጠት ቀጥሎ ከመሃከላቸው መልምለው የውሃቢዝምን ስልጠና ይሰጡ ነበር። ዛሬም ከሚጉዋዙት መካከል ይህንኑ ሁለት አላማ ለማከናወን ይጠቀመባቸዋል ሰልጥነው የሚመለሱትም ቢሆኑ ያንኑ የዱሮውን ተልኮ እንዲፈጽሙ ያደርጉዋቸዋል።

በዚህ በጣሊያን ወረራ ወቅት የሳዑዲ አክራሪዎች የሃረሪ ተወላጅ ከሆኑ የእስልምና መምህራን ጋር ጥብቅ ትስስር ፈጥረው ሃረርን መሰረት አድርገው እስልምናን የማስፋፋት ተልእኮ የመሩት ሼክ ዩሱፍ አብዱል ረህማንና ሃጂ ሰይድ ኢብራሂም ናቸው እነዚህን ስዎች በ1930 ዓም ወደ ሳዑዲ አረቢያ በመጉዋዝ የውሃቢያን አመለካከት በመውረስ ሃረርና መላ ኢትዮጵያ ውስጥ ወሃቢነትን ለማስፋፋት ተልእኮ ተቀብለው ተመልሰዋል።

አሁን ሃረር ውስጥ የሚታየው ሃይል የቀላቀለ እርምጃ የሚወሰደው ኢትዮጵያዊን ከዜግነቱ አንጻር ማየት ትተው ከሃይማኖቱ አንጻር ህገ መንግስቱን በመሳሪያነት ለመጠቀም እየተፈለገ ያለው የዚህ ውጤት እንደሆነ መገመት ይቻላል ይህንን ሁኔታ በሁለት መንገዶች ወደፊት እንመለከተዋለን።

መ. <u>የዚያድ ባሬ ወረራ</u>

ታላቋ ሱማሊያን እገነባለሁ በሚል ሺፋን እስልምናን በኢትዮጵያ ላይ ለመጫን በ1969 ዓ ም ኢትዮጵያን የወረረው የዚያድ ባሬ መንግስት ሳዑዲ ዐረቢያ በአጋዥነት በረሃ ውስጥ የአጋዥነን ሶማሌ ነጻ

አውጪ ድርጅቶችን መመስረትዋን ተከትሎ የወጣ ወታደራዊ ስልት ነበር። ጊዜውም ጥር 6 1968 ዓ.ም በአለም ሙስሊሞች ሊግ በኩል ኦሮሞዎችን ያቀፈውና የምእራብ ሶማሌ ነጻ አውጪ ግንባርን እንደገና የማዋቀር እንቅስቃሴ ዓላማ የአካባቢው ፓለቲካዊ ነጻ መውጣት ሳይሆን በባሌ በአርሲና በሲዳሞ የሚገኘውን ሙስሊም ለማንቀሳቀስ የታለመ ነበር። በዚህ ድርጅት መቋቋም የተደፋፈረው የዜያድባሬ መንግስት ጦር ኢትዮጵያን ወርሮ ክፉኛ ተመትቶ ወጥቶአል።

II. <u>ወሃቢያና ወሃቢያዊ ፍልስፍና(ሃይልን የቀላቀለ አካሄድ) መቼና እንዴት እንደ ተጀመረ</u>

በመግቢያዬ ላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት የወሃቢያ ፍልስፍና ሥረ መሠረቱ ዐረባዊነትንና የዐረብ ባህል የበላይነትን ለማስፈን የተጀመረ ፍልስፍና ነው። እየቆየ ሲሄድ ግን የተጀመረበትን ዓላማ ለቆ የሃይማታዊ አክራሪነትን መርህ በመከተል ከዐረባዊ የባላይነት ፍልስፍና ወደ አስላማዊ ሃይማኖት የበላይነት ፍልስፍና ተሸጋገረ። ይህ የበላይነት የሚመጣው በጅሃድ እንደሆነ ስለሚያምን በጅሃድ በማስገደድ የዓለም ሃይማኖቶች ሁሉ ወደ እስልምና እንዲለወጡ ማድረግን የፍልስፍናው ማስፈፀሚያ መሳሪያ አድርጎ ለመጠቀም በመወሰን ተግባር ላይ አዋለው ለዚህም ድጋፍ የሚሰጡትን ቁርአናዊ ጥቅሶችን ማየት ይቻላል።

1. ሱረቱ አል-ባቅራ 2:256 ‹‹በሃይማኖት ማስገደድ የለም›› ብሎ እስላም የሰላም ሃይማኖት ነው እያለ <u>*በአፉ ይሰብክል ነገር ግን*</u>

2. ሱረቱ አል-አናፋ 8:39 ‹‹ሁከት እስከማትገኝ ሃይማኖት ሁሉ ለአላህ ብቻ እስኪሆን ተጋደሉአቸው›› ይላል።

3. ሱረቱ አል-ተወባህ 9:29 ‹‹አላህንና መልዕክተኛውን (መሐመድን) እርም የሚያደርጉትንና እውነተኛውን ሃይማኖት (እስልምናን) የማይቀበሉትን እነርሱ የተዋረዱ ሆነው ግብር በእጆቻቸው እስኪሰጡ ድረስ ተዋጉአቸው›› በዚሁ ምዕራፍ ቁጥር 5 ላይ ‹‹ባገኛችሁበት ሥፍራ ግደሉቸአው›› ይላል።

4. ሱረቱ አል-አሣእ 4:59 ያዙአቸው ማርኩአቸው ባገኛችሁበትም ሥፍራ ግደሉአቸው ከእነርሱም ወዳጆችንና ረዳትን አትያዙ›› እያለ እንዲገድሉና ክርስቲያንና ሙስሊምን በአንድ ላይ እንዳይኖሩ መጽሐፉ ራሱ ያዛቸዋል።

በተራ ቁጥር አንድ ላይ የተጠቀሰው "በሃይማኖት ማስገደድ የለም የሚለውና በተቀሩት ሶስት ቁጥሮች መካከል የቅርጽ እንጂ ምንም የይዘት ልዩነት እንደሌለው የሃይማኖቱ ምሁራን ያስቀመጡትን መመልከት እንችላለን። "Belteshazzar and Abdnego" የተባሉ ደራሲያን "the Mosqeu and its Role in Society" በተሰኘው መፅሐፋቸው በሃይማኖት ማስገደድ የለም የሚለውን በሚከተለው ሁኔታ ገልፀውታል " the Issue of no compulsion in religion often quoted by muslims when freedom of religion is discussed is a convenient phrase. This and others similar verses that Muhammad o stated earlier have all been abrogated and replaced by later revelations. . .

If there is no compulsion in religion and that was indeed true why does the Saudi Arabia penal code presirbe a death penalty to any muslim with in Suadi Arabia were he to change his religion? why is Abdul Rahman the Afghani, convert in prison facing a death sentence for his

conversion to Christianity? why was mehdi Debaj assassinated by Iranian government agents for converting to Christianity? why do the Iranian authorities persecute those who Convert to Baahiisem? Almost any where in the Islamic world. A public statements of Muslim's convert in or discarding of islam bears heavy penality, of isolation, offical persecution, imprisonment and even death.

እንደነዚህ የሃይማኖቱ ምሁራን አገላለጽ በቁርአን ላይ የተጻፈውና በተግባር የሚፈጸመው ፉጹም የተለያየ መሆኑን እንገነዘባለን። ሰውን እያስገደዱ ማስገደድ የለም ሰውን እየገደሉ እስላም ማለት ሰላም ማለት ነው የሚባሉ አባባሎቸ እውነት ያለመሆናቸውን አንባቢ ሊፈርደው ይችላል።

ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችን ለመቀስቀስ ሲባል በተዘጋጀ ሲዲ ላይ «ክርስቲያኖችን በሉአቸው፤ከፈለግን ጀሀድ በሀገሪቱ ማወጅ እንችላለን፤ ቤተክርስቲያኖችንም እንደ ችቦ አንድዱአቸው... ወዘተ በማለት ተናጋሪው ያደረጉትን ንግግር የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ ጣቢያ ሰኔ 8 ቀን 2004 ዓ.ም ለአወሊያ ት/ቤት ንቅናቄ አስተባበሪ ኮሜቴ አባላት በቃለምልልሱ አስደምጦ ነበር ጋዜጠኛውም አያይዞ ሲጠይቀው እዚህ አሁን የሰማነውና የናንተን ንቅናቄ እንዴት ያስተያዩታል በማለት የኮሚቴውን አባል ጠየቀው ሰውየውም ሲመልስ እስልምና የሰላም ሐይማኖት ነው ሰዎችን አይገድልም አሁን የሰማነው ሰው ሀሣብ ግን እስልምናን አይወክልም ይሄ የግለሰብ ስሜት ነው ሲል መልስ ሰጥቷል» በኢትዮጵያ፣ በሱማሊያ፣ በኢራቅ፣ በአፍጋኒስታን፣ በፓኪስታንና በሕንድ የብዙ ሺ ሰዎችን ሕይወት የሚያጠፋው ታዲያ ማን ይሆን?

ስለዚህ ለዚህ ትምህርት የሚገባው ወሃቢያ ትርጉሙ ጀሃዳዊ አክራሪነትን የሚከተል ፍልስፍና መሆኑን ከተግባሩ መረዳት ይቻላል።

ይህ ፍልስፍና ወደ አፍሪካ እና ከሁሉም በላይ ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት ሺህ ዓመታት የፈጀበት ሲሆን ከዛሬ 20 ዓመት በፊት ግን በተፈጠረለት እድል ሳቢያ ሙሉ በሙሉ እንዲት እንደገባ ለማየት እንሞክራለን።

እስከ 1982 ዓ.ም ድረስ ንቁ ያልነበረው ኢትዮጵያዊ እስልምና ከዚህ ጊዜ በኋላ መነቃቃት የጀመረው የ24 ሙስሊም ሀገሮች መሪዎች በአባልነት የሚገኙበት ማህበር ናይጀሪያ አቡጃ ላይ በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ1989 ዓ.ም (1982/1983 በኢት.አቆጣጠር) ተሰብስበው *Islam in Africa Organization* የተሰኘ ድርጅት ከመሠረቱ በኋላ ነው። መሥራቾቹ ለዚህ ማኅበር ሥራ ማንቀሳቀሻ 21 ቢሊዮን ዶላር መድበው ነበር። *IAO*. ከተመሠረተ በኋላ መሪዎቹ ከወሰኑአቸው በርካታ ውሳኔዎች አንዱ እንዲህ የሚል ነበር። «በአፍሪካ ውስጥ ያሉ ሀገሮች ሙስሊሞች በሙሉ የሸሪያ ሕግ ተፈፃሚ እንዲሆን አስፈላጊውን ጥረት እንዲያደርጉ ማኅበሩ (IAO) ደግሞ ከጎናቸው ሆኖ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል የሚል ነበር። IAO በተመሠረተበት ወቅት ኢትዮጵያ ሀገራችን የመንግስት ለውጥ ያደረገችበት ጊዜ በመሆኑና አዲሱ መንግሥት ከሚከተለው የሃይማኖት ፖሊሲ ጋር ነገሮች ስለተጣጣሙ በአፍሪካ ውስጥ መስፋፋት የጀመረው ወሃቢያዊ ፍልስፍና በኢትዮጵያ መተግበር ተጀመረ። በተለይም ባለፉት አስር ዓመታት በስውር መዋቅሩን ዘርግቶ ሲደራጅ ከቆየ በኋላ በእነሱ አጠራር *«እስልምና በኢትዮጵያ ከመታገስ ወደ መታገል ተሸጋግሯል»* በሚሉት ዘይቤ ከአስተኛ ትንኮሳ እስከ ሽበር ፈጠራ ድረስ በማደግ በሚስጢር ከሚሠራበት ወደ ይፋ እንቅስቃሴ ተሸጋግሯል። ባለፈው ጥርና የካቲት ወር 2004ዓ.ም

በመላ ሀገሪቱ የተደረገው መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ ለዚህ ማረጋገጫ ነው።

በዚህ ምቹ የዲሞክራሲ ሥርዓትና የሃይማኖት ፖሊሲ በኢትዮጵያ ውስጥ ሥር እንዲሰድ ለሚፈለገው የወሃቢያ ዕንፈኛ ፍልስፍና የጀርባ አጥንት የሆነችው ሳዑዲ አረቢያና ሌሎች የመካከለኛና የደቡብ ምስራቅ እስያ ሀገሮች በሃይማኖቱ፣ በማኅበራዊው፣ በፖለቲካውና በኢኮኖሚው ዘርፍ የእምነቱን አራማጆች በማጠናከር ተረባርበው መሥራት ጀመሩ። ይህን እቅድ ለማስፈፀም በዋናነት የዓለም ሙስሊም ሊግ የተባለ ድርጅት ኃላፊነቱን ወሰደ። የተለያዩ እስላማዊ እርዳታ ድርጅቶችን እንዲያቋቁም ተደረገ። ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያስችሉትን የሳዑዲ *«እስላማዊ ዓለም አድን»* ድርጅትንና *«አል-ሀረማይን»* ድርጅቶችን አቋቋመ። ወሃቢያን ማጠናከር እንዲሁም ሌሎች ተጨማሪ ድርጅቶችን አቋቁሞ ለመሥራት ባለፉት 20 ዓመታት ዕንፈኛውን ወሃቢያ ዛሬ ለደረሰበት ተልእኮ መፈፀም አብቅቶታል። እነሆ ባለፉት 10 ዓመታት ደግሞ «ከመታገስ ወደ መታገል ተሸጋግሮ» የማጥቃት ሥራ በመፈፀም እስላማዊ መንግስት በኢትዮጵያ ለማምጣት በዕናት እየሠራ ይገኛል። በተለያዩ የሀገሪቱ ክልል ከተሞች የተፈፀሙት መጠነ ሰፊ ጥቃቶች ዕንፈኛው ቡድን የደረሰበት የመጀመሪያው የእድገት ምዕራፍ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ይህ እድገት ቀጥሎ ከጥር እስከ የካቲት ወር 2004 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት መዋቅሩ ስለፈረሰበት በውጭ ሚዲያዎች፣ ቢጋዜጠኞችና በመጽሔቶች እንዲሁም ድረገጾችን በመጠቀም መንግስትን እስከማብጠልጠል ደርሰዋል። ይህም መቻቻልን የሚደግፉ በሃላፊነት

ላይ ያሉትን የእስልምና መሪዎችን በአክራሪው በመቀየር መቻቻልን በተቋም ደረጃ ለማጥፋት እየታገሉ ይገኛሉ።

III. ወሀቢያ ኢትዮጵያ ውስጥ ለማደግ የሚጠቀምባቸው ስልቶች

አክራሪ እስልምና ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ የመጣ ኃይማኖት ነው።በኢትዮጵያ ከ1983 ዓ.ም ወዲህ እያደገ እንዳለና ለዕድገቱም የሚጠቀሙ ልዩ ልዩ ስልቶችን በሥራ ላይ አውሏል እነዚህን ስልቶች አንድ በአንድ እናያለን።(ማደግ ማለት ከቀድሞ የተሰየ ለካሄድ ስማለት ነው)

ሀ. ሐይማኖታዊ መልኮች

1. ስራውን የማደራጀትና የመምራት ስልት

ተከታዮቹን በልዩ ልዩ ዘርፍ በመከፈል ለዕደገቱ አስተዎጽኦ እንደያርጉ ያግዛል ለዚህም ተከታዮቹን በአምስት ከፍሎአቸዋል።

1.1 የተማሩ ሰዎች አገልግሎት፡- ይህ አገልግሎት የተማሩ ሰዎችን በምሁራን የመድረስ አገልግሎት ነው።

1.2 የታምራት አገልግሎት፡- ከሱዳን በሚመጡ መተተኞችና ረጋሚዎች ምድርንና ቤተክርስቲያንን ቅዱሳንን ማስረገም ነው።በየመንደሩ ተዘዋውረው ከፍታ ላይ ቆመው ሲረግሙ ማስተዋል ይቻላል።

1.3 የነጋዴዎች አገልግሎት፡- የእስልምናን ዕድገት በገንዘባቸው እንደደግፉ ሀላፊነት ወስዷል።

1.4 የተራው ሕዝብ አገልግሎት፡-ይህ አገልግሎት ብዙ ሚስቶችን በማግባት ብዙ ልጆችን እንዲወልዱ ማድረግ ሲሆን ክርሲቲያኖችን እንዲያገቡ የሚበረታቱበትም አገልግሎት ነው። በ1997 ምርጫ ወቅት በክሊኒኮች ላይ በተደረገ ጥናት እስከ 58% እርጉዞች የእስላም ሴቶች እንደነበሩ ጥናት

አመልክቷል ሌላው ተመሳሳይ ስልት ደግሞ በ1998ዓ.ም አካባቢ ማህጸን መከራየት የተባለ ስልት ነው ሴቶችን ሲያገቡ ገንዘብ እየሰጡ ልጅ እንዲወልዱ ማድረግና ልጅ ሲወለድ አሳድጎ ልጅን መረከብ ነው። ይህ ስልት በሰሜኑ የሃገራችን ክፍል በሚስጥር ይጠቀሙበታል።

1.5 የኃይማኖት አስተማሪዎች ዘርፍ፡- የደእዋ አገልግሎት

በመባል ይታወቃል የማስተማር፣ የማስልጠን፣ ደቀመዝሙር የማድረግ ኃላፊነትን ይወስዳል። አባሎቹን ሁለት ሁለት በማድረግ ወደ ክልሎች ማሰማራት አባላትን መሳበኘት ህዝቡ ወደመስጊድ እንደሄድ ያበረታታሉ ከእስልምና ወደክርስትና የተመለሱትን ተከታታሉ ወደ እስልምና እንዲመለሱ ማድረግ ከተግባራቸው መካከል ይጠቀሳል።

2. የህትመትና የስርጭት ስልት

ከ1983 ዓ.ም ወዲህ የህትመቱ ዘርፍ ለፕሮፓጋንዳ መጠቀሚያነትና ለማስተማርያ መረጃነት እንደጠቅም ተደርጎ ተደራጅቷል። እስላማዊ ጋዜጦችና መጽሄቶች እየታተሙ ገበያ ላይ ውለዋል። ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥራቸው እየጨመረ መጥቷል ለምሳሌ እንደ ቢላል መጽሔት፣ የሙሲሊሞች ጉዳይ የሚባል መጽሔት፣ የሚጠቀሱ ሲሆን አልቅዱስ፣ ሠለፊያ፣ ሠውቱል እስላምና ኢትዮ እስለም የሚባሉ ጋዜጦች እስልምን ለማስተማር ይጠቀሙባችዋል። ቁርአንም ወደ አማርኛ ተተርጉሞ መሰራጨት ጀምሮአል። ልዩ ልዩ ሀይማኖታዊ በራሪ ወረቀቶቻችም እያሳተሙ ያሰራጨሉ። እነዚህ ጋዜጦች በዓለም ዙሪያ የሚደረገውን የእስልምና የፕሮፓጋንዳ ሥራ ይሠራሉ። ክርስትናንና ክርስቶስን በማንቋሸሽ የሚሰሩ ህትመቶች በራሪ ወረቀቶች እየተዘጋጁ ይሠራጫሉ። ከዚህ ሌላ በየጋዜጣው ላይ ቁርአን ተቃጠለና ተቀደደ የሚል በየሳምንቱ አንድ ዜና የማይጠፋ

ሲሆን ዜጎችን ከሙስሊሞች ውጪ ያሉትን ክርስቲያኖች ሳይሆን ካፊሮች ሲሉ በመጥራት መስለም አለመሆንን ወንጀል አድርገው እስከመግለጽ ድረስ ጋዜጦቻቸው አዘውትረው ይፅፋሉ።

ከዚህ ሌላ ቁርአን ለመጀመሪያ ጊዜ በአማርኛ በክፍል ተከፋፍሎ ከነማብራሪያው ታትሞ ለስርጭት በቅቷል። በነጃሽ ማተሚያ ቤት እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ ከ71 በላይ መጽሐፍት ተዘጋጅተው ተሰራጨተዋል አንዳንድ ህትመቶች ደግሞ ለሐይማኖታዊ ቅስቀሳ በክልል መንግስት በጀት ስፖንሰር ተደረገው እንደተሰራጩ ተመልከተናል። ለምሳሌ የሃረሪ ክልላዊ መንግስት በጀት ለዚህ ተጠቃሽ ነው። ህዳር 1994 ቅጽ 1 መብቱ የሃረሪ ጉባኤ እንደሆነ የተገለጸበት መጽሐፍ በሜጋ አሳታሚ ድርጅት የታተመ ሲሆን በሀረሪ ክልላዊ መንግስት ወጪ መሸፈኑ ዋናው ታሪክ ከተጻፈበት ፈረንሳይኛ ወደ አማርኛ የተመለሰው አብዱላ መሃመድ አሊ የግራኝ አሕመድን ወረራ ገልጻው በመቅድሙ ላይ «ለዚህ ትውልድ» ያለውን ጠቀሜታ በማስፈር ወታደራዊ እስትራቴጂ መታሰብ ያለበት ለዚህ ዘመን መጥቀሙን ጭምር የሚገልጽ ነው። (ከገፅ 2-6) በተመሳሳይ ሁኔታ በሃረሪ ክልላዊ መንግስት ስር በክርስቲያኖች ላይ የሚደረገውን ጥቃትና ህገመንግስታዊ መብቶች ያለመፈጸማቸው ከእንደዚህ አይነት ሁኔታ ጋር ተያያዥነት እንዳለው መጠርጠር ይቻላል።

በሐረሪ ክልል ለሚያጣውን የክርስቲያኖችን አቤቱታ ክርስቲያን ኮንሰርን የተባለ የመብት ተሟጋች ድርጅት የዘገበውን ቃለ ምልልስ እንመልከት።

ሀ. በጨለንቆ ወረዳ በአንድ ግለሰብ የተወሰደን የቀብር ስፍራ ለማግኘት ሰባት አመታት አልፈዋል እስካሁንም አልተመለሰም።

"የኢሕአዴግ መንገድ የጠራ ስለሆነ ህ/ብ የበደልን ከሆነ ለምን ድጎ ነው መንግስት እኛን ያልጠየቀን፣የወረዳው አስተዳዳሪ የተናገሩት"

"400 ክርስቲያኖች ፒቲሽን ፈርመን የተወሰደብን የቀብር ስፍራ ይመለስልን ወይም በልዋጩ በአቅራቢያችን ይሰጠን ስንል ሰባት አመት አለፈን" የጨለንቆ አካባቢ ክርስቲያኖች የተናገሩት

"ጉዳዩን እንዲያጠኑ አጥኚዎች ልከናል ስለዚህ ለጉዳዩ ባለቤቶች ሁኔታውን አስረዳለሁ" አቶ አሰግድ ምሰራቅ ሃረርጌ ዞን ጉዳዩን በቀርበት የሚከታተሉ ባለስልጣን የተናገሩት።

ክርስቲያኖች በዚህ ወረዳ ውስጥ የቀብር ስፍራ እንዲሰጣቸው አመልክተው ከ12 አመት በፊት የቀብር ስፍራ ተሰጥቷቸው ነበር። ለነርሱ በተሰጠው ቦታ ላይ ሰላሳት አመት ከተጠቀሙበት በኋላ አስራ አምስት ሰው ያህል ተቀብሮበት ነበር ይህ በአንዲህ አንዳለ አንድ ሰው ይመጣና በስፍራው ላይ ጫት ይተክላል ጎጆ ቤትም ይሰሩበታል ክርስቲያኖች መቀበሪያ ቦታ አጣን ይላሉ። ያውም አካባቢው በተራራ ስር ስለነበር ድንጋያማ ስለሆነ የሚመጣው ጎርፍ አስከሬኖችን የሚያጥብ ሲሆን ፈጽሞ አዋራጅ ድርጊት ከመሆኑም በላይ ቀብረን ለመመለስ ጠዋት ወጥተን ማታ መመለስ ነበረብን" ይላሉ። የአካባቢው ቤተክርስቲያን መሪዎች ይህ እኛን የቀብር ስፍራ የማሳጣት ነው ስንል ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ልዩ ልዩ ተቋማት አቀረብን መልስ ስናጣ ጎዳዩን ለምስራቅ ሃረርጌ አስተዳደር አመልክተን ሶስት ጊዜ ሰዎች ተመድበው አጥንተው አሁን ውሰዱ የሚሉንም ሆነ በግለሰቡ ከተከለለው ውጪ ያለው ለቀብር እንደማይሆን የገለጹ ሲሆን ይህ ቆይታ ያለመፍትሄ ሰባት አመት ሞላው እናም ተበድለናል ፍትህን ማግኘት አልቻልንም ሲሉ በአካባቢው ያሉ ክርስቲያኖች ይናገራሉ።ሰሙስሊሞች በከተማው ዙሪያ አምስትና ስድስት ቦታዎች ነው የሚሰጣቸው። በማለት ተበዳዮቹ ክርስቲያኖች ለክርስቲያን ኮንሰርን ገልፀዋል።

የቀብር ስፍራ ማጣት የዜግነት መብትን መንፈግ አይደለም ወይ ሲል የክርስቲያን ኮንሰርን ተወካይ ጠይቆ ነበር

"የወረዳው አስተዳደር አቶ ,ሽምሰዲን ኢስማኤል ግን እኛ ቦታ ስጥተናቸው አንወስድም ብለውን ነው ከፈለጋችሁ የሰጠናቸውን ቦታዎች መጥታችሁ እዩ የኢሃዴግ መስመር የጠራ መስመር ስለሆነ ህዝብን ማጉላላት አንፈልግም" ሲሉ ይገልጻሉ ባይሆን ኖሮ ሰምን ድን ነው መንግስት የማይጠይቀን ሲሉ በመንግስት አሰመጠየቃቸውን እንደማስረጃ ይጠቅሳሉ።

ክርስቲያኖቹ ግን በዚህ ሃሳብ አይስማሙም የምስራቅ ሃረርጌ የዞኑ ኃላፊዎች ተደዋውሰው እዛ ሲመጣልህ እሰረው እስከማለት መድረሳቸውን በተደራጀ መልኩ ከዞንና ወረዳ ተመሳጥረው ሆን ብለው ሃይማኖታዊ ጥቃት ለማድረግ ከመፈለግ እንጂ ለእኛ ሲሆን ነው ወይ የቀብር ስፍራ የሚጠፋው? ሲሉ ይጠይቃሉ ቀብረን እስክንመለስ 4 ሰአት የእግር ጉዞ የሚፈጅ ቦታ ነው አዘጋጀሁ የሚለው ? ጉዳዩን ለማጣራት የመጡትም ሆነ በከተማው ውስጥ ይሰሩ የነበሩት ሰራተኞች ወረዳ አስተዳደሩ የቀብር ስፍራ ሰጠሁት የሚለው ይህንን ያህል ርቀት ሄደን እኛ እንኩዋ በመኪና ሄደን የራቀበትን ስፍራ ነው ወይ ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል ይላሉ።

በዞኑ አስተዳደር በሶስተኝነት ደረጃ ላይ ያሉ አቶ አሰግድ ደግሞ ስፍራውን የሚያጠና ሰዎችን ልከናል አሁን የምናገረው ለጉዳዩ ባለቤቶች እንጂ ለሚዲያው አይደለም ሲሉ ለክርስቲያን ኮንሰርን ገልፀዋል።

የተሰጣችሁን ቦታ ለምን አልወሰዳችሁም በማለት ለክርስቲያኖች ለቀረበው ጥያቄ አንደኛ የቤተክርስቲያን አገልጋይ እንዲህ አይነቱን ሆን ተብሎ በመንግስት ስልጣን ሃይማኖታዊ ጥቃት መፈፀም በደንብ የሚገባን ጉዳይ ነው ቢያስፈልግ የበፊቱን ቦታችንን አንድ ግለሰብ ሲወስድብን በስፍራው ጫት ሲተኩሱበት ቤቶች ሲሰሩበት መንግስት ይህንን ማስጣል አልመቻሉ ላለመስጠት ያለውን

ቱርጠኝነት የሚያሳይ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ በልዋጩ ሊሰጠን የተመረጠው ቦታ ደግሞ ከአካባቢያችን ደርሶ መልስ 4 ሰአት የሚፈጅ መሆኑ ከዚህ በተጨማሪ ከከተማ ወጥተን የገበሬ መንደርን አቁዋርጠን እንድንሄድ የሚያደርግና ጊዜን አትምን ያላገናዘበ ሲሆን ሴቶች ለቀብር መሄድ እንደሚገባቸው የክርስቲያኑን እምነት ፍላጉት ያላገናዘበ እርምጃ ሲሆን ጉዳዩን እንዲያጠኑ ከምስራቅ ሃረርጌ የተላኩትም ቢሆኑ ለቀብር የማይሆን መሆኑን አጥንተው ተመልሰዋል ስለዚህ አቶ ሽምሰዲን ሌላ ፍላጎት እንዳላቸው እንገነዘባለን የከተማው የቦታ አስተዳደር አራሱ አቶ ሽምሰዲን እስማኤል ቢፈቀድ ሊሰጥ የሚችልበት እድል እንዳለ እንሰማለን" ሲሉ ክርስቲያን ኮንሰርን ያናገራቸው የቤተክርስቲያን መሪዎች ተናግረዋል።

የቀብር ስፍራ ተወስዶብን ከዚያም ለቀብር የሚመች በአቅራቢያችን ይሰጠን ስንል ጥያቄ ያቀረብን ፒቲሽን ተፈራርመን ያስገባነው አራሱ 400 ሰው ያህል ነው። መቅበሪያ ቦታ የለንም።በማለት የደረሰባቸውን ክርስቲያኖቹ በምሬት አስታውሰዋል።

የቤተክርስቲያን ንብረት የወሰዱትን ደግሞ ክርስቲያን ኮንሰርን የዘገበውን ተጨማሪ በደል እንመልከት

ሰ. በሃረሪ ክልል በሃረር ከተማ በፖሊስ የተወሰደ የቤተክርስቲያን ንብረት እንዲመለስ ሲጠየቅ ሁለት አመት አለፈው!

ንብረቱን የወሰደው ሰው አራሱ አቃቢ ህግ ነው ስሙ ሸኪር አህመድ የተሰኘ ሰው ነው የአካባቢው ክርስቲያኖች የተናገሩት

ድርጊቱን የፈጸመው ሰው ወደ ጅጅጋ ሄዶአል በሙያው ግን አቃቢ ህግነው የሃረሪ ክልል ፖሊስ ኮሚሺን የወንጀል መከላከል ክፍል ሃላፊ በ 2010 የሩሲካ ትንሳኤ በአልን ለማክበር በመኪና መሳታወቂያ ለመንገር ከከተማው ጽህፈት

ቤት ፍቃድ በመውሰድ የክሉሉ ፓሊሶችን መኪና ላይ አድርገው አይሱዚ መኪና ተከራይተው በመኪናው ላይ በተጫነ የድምጽ መሳሪያ ማስታወቂያ በመንገር ላይ ነበሩ። በመሃከል «በሃረሪ ቋንቋ ስለ ኢየሱስ ሲናገሩ ስለ ኢየሱስ በሃረሪ ቋንቋ መናገር አትችሉም» ብለው ሲቪል ልብስ የለበሱ ፓሊሶች ክርስቲያኖችን ከደበደቡአቸው በኋላ ስድስቱን የአስር ቀን ጊዜ ቀጠሮ ወስደው አስረዋቸዋል። ይሁንና በአጋጣሚ የፌደራል ጉዳዮች ባለስልጣን የሆኑ ሰዎች በከተማው የነበሩ ስለነበር ይህ የዜግነት መብት ነው እንዴት እንዲህ ይደረጋል ሲሉ የታሰሩትን ሰዎች ፈቱዋቸው። ይሁንና መኪናውን ያከራየው እና ረዳቱም ሙስሊሞች ስለነበሩ እንዴት ክርስቲያኖች እንዲጠቀሙበት መኪና ታከራያላችሁ ተብለው የተደበደቡ ሲሆን የጫነውን ሙሉ መሳሪያ ወደ ጀጎል በመውሰድ ንብረቱን አላየንም ሲል መለሱ ። አስገራሚው ጉዳይ መሳሪያውን የወሰደው ሰው ብሙያው በስራ ላይ ያለ አቃቢ ህግ ሲሆን ጉህም አካሄድ ሃራሪ ክልል ፓሊስ መምሪያ እንደማያስኬደው ባረጋገጠ ጊዜ የተወሰነውን ንብረት ቀንሰው ዘራፊ ወስዶት ነበርና በማለት የቀረውን ንብረት ውሰዱ ተባሉ። ቤተክርስቲያን ግን ፓሊስ አሁን ሊሰጥ የፈለገው ከዘራፊዎች ከሆነ ዘራፊዎች ለህግ ይቅረቡ ስትል ጠየቀች። ይሁንና ፓሊስ የተቀበለውን ንብረት ይዞ የገባውን ንብረት ዘራፊዎች ወስደውት ነው የሚለው ፈጽሞ ከእውነት የራቀ ድርጊት ሲሆን ከአንድ መንግስታዊ ተቋዋም የማይጠበቅ ነው። ይሁንና ድብደባና እንግልት ከመፈጸማቸው በተጨማሪ እስካሁን 50 ሺ ብር ግምት ያለው የሙዚቃ መሳሪያና 7 ሺ ብር ግምት ያለው የድምጽ መጠን መመጠኛ ዲክና ተያያዥነት ያላቸው የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን እስካሁን ለቤተክርስቲያን አልተመለሱም ሲሉ የቤተክርስቲያን መሪዎች ይናገራሉ ።

የክልሉ ፓሊስ ኮሚሽን የወንጀል መከላከል ክፍል ሃላፊ የሆኑት ሰው ስለጉዳዩ ተጠይቀው "ጉዳዩ በመርማሪ ፓሊስ እጅ ያለ ሲሆን ወደ ውሳኔ ለማምጣት እየሰራን ነው ድርጊቱን የፈጸመው ሰው አሁን በአካባቢው የለም ጅጅጋ ሄዷል" ሲሉ የገለጹ ሲሆን ከዚያው አካባቢ ጉዳዩን የሚከታተሉት የቤተክስቲያን መሪዎች ግን አቃቢ ህጉ አሁንም በስፍራው አሉ ቢሮአቸው አሉ ሁለት አመት ሙሉ ፓሊስ ህግ ለማስጠበቅ የሚፈልግ ቢሆን ኖሮ እስካሁን ምን ይሰራል ሲል ይጠይቃሉ።

ወሳጆች በህግ አልተጠየቁም በድርጊቱ ግን የዞኑ ፓሊስ መምሪያው አራሱ እጁ ያለበት ሲሆን የመጀመሪያውን ድብደባ አድርገው መኪናውን ይዘው እቃውን የወሰዱትም እነርሱ ናቸው ይላሉ። ለዚህ ነው አሁን መፍተህሄ መስጠት የተቸገሩት ሲሉ የክልሉ ንብረት የተወሰደባቸው ቤተክርስቲያን መሪዎች ይገልጻሉ። የሃረሪ ክልል ፓሊስ ኮሚሽን፤ ለእንባጠባቂ ተቋዋም አመልክተን ነበር። ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጥበቃ ኮሚሽን ለሃረሪ ጎዝብ ክልላዊ መንግስት አመልክተናል ሃይማኖታዊ አክራሪነት ና ህገመንግስታዊ መሰረቱን በማቀላቀል ክርስቲያኖችን ለማጥቃት መንግስታዊ መዋቅሩን ይጠቀማሉ ይላሉ ። "ጉዳዮን ለበላይ የመንግስት አካል ለማመልከት ጨፌ ኦሮሚያ ጽህፈት ቤት ለኢህአዴግ ጽኅፈት ቤትም አመለክተናል። ጉዳዩን ሊመለከቱ ይገባቸዋል ለተባሉ ተቋዋማት አመልክተናል። ፍትህ በአደባባይ የሚካድበት ክርስትና በመንግስት መዋቅር ጥቃት እየተደረገበት መሆኑን በተጨባጭ የሚያሳይ ነው" በማለት የቤተክርስቲያን መሪዎች አረጋግጠዋል።

ጠባቂ ተቋዋም አመልክተን ነበር። ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጥበቃ ኮሚሽን ለሃረሪ ጎዝብ ክልላዊ መንግስት አመልክተናል ሃይማኖታዊ አክራሪነት ና ህገመንግስታዊ መሰረቱን በማቀላቀል ክርስቲያኖችን ለማጥቃት መንግስታዊ መዋቅሩን ይጠቀማሉ ይላሉ ። "ጉዳዮን ለበላይ የመንግስት አካል ለማመልከት

ጨፌ ኦሮሚያ ጽህፈት ቤት ለኢህአዴግ ጽ/ፈት ቤትም አመለከትናል። ጉዳዩን ሊመለከቱ ይገባቸዋል ለተባሉ ተቁዋማት አመልክተናል። ፍትህ በአደባባይ የሚካድበት ክርስትና በመንግስት መዋቅር ጥቃት እየተደረገበት መሆኑን በተጨባጭ የሚያሳይ ነው" በማለት የቤተክርስቲያን መሪዎች አረጋግጠዋል።

እንግዲህ ሙስሊሞች በሚበዙባቸው ክልሎች እነዚህና ከነዚህም የከፉ የመብት ጥሰቶች እንደሚካሄዱ በርካታ ጥናቶች አረጋግጠዋል ታዲያ እዚህ ሀገር የሐይማኖት እኩልነት በተረጋገጠባት ኢትዮጵያ እየተተገበረ ያለው የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ 27 ነው ወይስ ሳናውቀው በስውር የታወጀ «የሼርያ ሕግ?» ወደፊት በሁለተኛው ዕትም እንደነዚህ ዓይነቶቹን በደሎች በዝርዝር እናቀርባለን።

3. የካሴት አገልግሎት ስልት

ቀድሞ ያልነበረ ዘርፍ ነው የሙስሊምና የክርስቲያን ክርክሮችን በኦዲዮና በቪሲዲዎች አሳትመው ያሰራጨሉ ክርስቲያን ለማንቋሸሽና ለመዘበቻ የታቀዱ ስብስቶችን ተሰርተው ይሠራጨሉ። ለዚህ ድርጊት ሲሉ በየከተማው በክርስትና እምነታቸው አዲስ የሆኑትን ወይም በቃሉ እውቀት የሌላቸውን አማኞች ለውይይት እንደሚፈልጓቸው ይነግሯቸዋል ከዚያም ክርክሩን የክርስቲያኖች የእምነት መጽኃፍ መጽኃፍ ቅዱስ ላይ ያደርጉታል ከዚያ የተመረጡ ጥቅሶችን ይጠይቃሉ ግራ መጋባቱን በቪሲዲ ያሰራጫሉ ይሁንና በዚህ ጉዳይ ላይ ይህንን በቅርበት የሚከታተሉ ሰዎች በሰአት የተከፋፈለ ውይይቱ በቁርአንም ሆነ መጽኃፍ ቅዱስ ላይ እኩል እኩል ሰአት መካፈልን ቁርአን ላይ ያሉትን መከራከሪያዎች ክርስቲያኖች በቂ እውቀት ይዘው መቅረባቸውን ቀጥሎም ውይይቱን የሚመሩ ገለልተኛ ዳኞች በቪሲዲ ቅጂዎች ደግሞ ሁሉም ወገኖች እንዲቀዱ ማድረግ በዚህ አይነት ጊዜ የመከራከር ስልት ቢጠቀሙ ክርስቲያኖች ተሸናፊዎች አይሆኑም።

4. የመሰጊድ ግንባታ ስልት

ይህ የኃይማኖት ዘርፍ አገልግሎት ቢሆንም ከ1983 ዓ.ም ወዲህ በእጅጉ እየተሰፋፋ ያለ ስልት ነው ግንባታው ሌላም ጠቀሜታ አለው ይኸውም የሥነ ልቦና ጫና ለማሰዳር ታስቦ የሚገነባ ነው። ምክንያቱም ምንም ተከታይ በሌለበት ቦታ ላይ መስጊድ ገንብቶ በውስጥ አንድ ቤተሰብ ማስቀመጥ የተለመደ ጉዳይ ነው። ከዚህም የተነሳ በአ.አ 150 መስጊዶች በመላው ሀገሪቱ ከ 20-30 ሺህ የሚገመቱ መስጊዶች መኖራቸውን መረጃዎች ይጠቁማሉ። በ1989 እንደ አውሮፓ አቆጣጠር I.A.O ውሳኔ መሰረት 50 ሙስሊሞች ባሉበት አንድ መሰጊድ እንዲገነባ ተወስኗል። ይህን ውሳኔ ተግባራዊ ለማድረግ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ምንም ሙስሊም በሌላባቸው አካባቢዎች በየአምስት ኪሎ ሜትር መሰጊድ ተገንብቶ እናገኛለን። ይህም ከኃይማኖታዊ ጠቀሜታው ባሻገር ለሥነ ልቦናዊ ጫና ጠቀሜታ እንዲውል ታስቦ የሚሰራበት ስልት ነው።

5. የመደበኛ ት/ቤቶች ግንባታ ስልት

የትምህርት ዘርፉ ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገበት ያለው በሰባት መልክ ነው።

5.1 በመዋዕለ ህፃናት

5.2 በህፃናት ማሳደጊያ

5.3 በአዳሪ ት/ቤት

5.4 በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች

5.5 በውጪ ሀገር ትምህርት

5.6በመድረሳዎች(የሃይማኖታዊ ት/ቤቶች)

5.7 የነፃ ትምህርት በሚሰጡ ት/ቤቶች

በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት የሃይማኖቱ ተከታዮች ከ95% በላይ ያልተማሩና እምነታቸውን እንኳ ጠንቅቀው የማያውቁ ከመሆናቸውም በላይ የባህል እምነቱን ከእስልምናው ጋር ደባልቀው የሚያመልኩ ናቸው። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ተከታዮች ደግሞ ለወሃቢያ አስተሳሰብ የማይመቹ ስለሆነ ሳዑድ ዐረቢያ በምትመራውና በምትደግፈው ዘርፍ ት/ቤቶችን በመገንባት ተማሪዎችን በወሃቢያ ጽነፈኛ አስተሳሰብ ማጥመቅ የረጅም ጊዜ ዕቅድ ሆኖ ተነድፏል። በአሁኑ ወቅት፦ በርካታ

5.1. *መዋዕለ ህፃናት፦* በመላ ሀገሪቱ ተከፍተው የዐረብን የባህል አለባበስ እንዲከተሉ በማድረግና ዐረቢኛን እንዲማሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ለጽንፈኝነት አስተሳሰብ ልጆችን እያዘጋጁአቸው ይገኛሉ። በአዲስ አበባ ከተማ እንደነ ኢቅራእእና ሌሎች የሚታወቁ መዋእለ ህጻናት ለዚህ ግብ ይሰራሉ።

5.2. *የህፃናት ማሳደጊያዎች፦* ወላጅ አልባ ህፃናትን እየሰበሰቡ በማሳደግና ለረጅም ጊዜ ዓላማዎቻቸው ለመጠቀም እየሠሩ ናቸው። ወላጅ አልባ የክርስቲያን ልጆች እንዲሰልሙ ለማድረግ ትኩረት ተሰጥቷል። በትምህርታቸው እየገፉ ሲሄዱ ወደ ውጪ ልከው ከፍተኛ የእስልምና ት/ቤት እንዲገቡ በማድረግ ለረጅም ጊዜ በጽንፈኝነት አስተሳሰብ ያጠምቋቸዋል።

5.3. *የአዳሪ ት/ቤቶችን መክፈት፦* ይኼኛው ስልት በቅርብ ጊዜ የተጀመረ ሲሆን ወሊሶ ላይ አንድ ት/ቤት ተከፍቶ ሥራ የጀመረ ሲሆን በተመሳሳይ ሁኔታ በሻሸመኔ፣ በሀገረ ማርያምና በሮቤ ላይ አዳሪ ት/ቤቶች እየተገነቡ ይገኛሉ። በክርስቲያን ተቋሞች የተቋቋሙት

አዳሪ ት/ቤቶች እየተዳከሙና እየተዘጉ ሲሄዱ አዳዲስ የእስልምና አዳሪ ት/ቤቶች መከፈታቸው ወደፊት ሊያደርስ የሚችለው ተጽእኖ ቀላል እንደማይሆን ከወዲሁ መገመት አያስቸግርም።

5.4. *መድረሳዎች (የመስጊድ ሃይማኖታዊ ት/ቤቶች)፦* እነዚህ ት/ቤቶች በመስጊዱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ያሉ ሲሆን ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ተማሪዎችን ይዘዋል። እነዚህ ት/ቤቶች የቀለም ትምህርትና የቁርዓን ትምህርትን አጣምረው የሚሰጡ ሲሆን ከትምህርት ሚኒስቴር እይታ ውጪ ናቸው። የትምህርት ፖሊሲው ት/ቤቶች ከሃይማኖት ትምህርት ነፃ ናቸው የሚለው አይሠራም። ስለዚህ በርካታ ተማሪዎችን በጽንፈኝነት አመለካከትና በማርሻል አርት በቴኳንዶ ስለጠና ተክነው እንዲወጡ የሚደረግበት ቦታ ጭምር ነው።

5.5. **የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የሚሰጡ ት/ቤቶች፦** እነዚህ ት/ቤቶች በሀገር ውስጥ ባለሀብቶችና በእስላም ሀገሮች ኢንቨስትመንት ሽርክና የሚካሄዱ ሲሆን በወሃቢያ አስተሳሰብ እነሱን ለመቅረጽ የተቻላቸውን ሁሉ እያደረጉ ይገኛሉ። ለምሳሌ ነጃሺ ኢትዮቱርክ ትምህርት ቤት ብንመለከት በአጭር ጊዜ ውስጥ እየተስፋፋ በመሄድ ላይ ይገኛል። አላማቸው የገባቸው ሰዎች ግን ልጆቻቸውን ከዚህ ት/ቤት እያስወጡ ናቸው።

5.6. **የነፃ ትምህርት የሚሰጡ ት/ቤቶች፦** እነዚህ ት/ቤቶች እስከአሁን ሥራ ላይ ያልዋሉ ሲሆን በ2005 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ 8 ነፃ ትምህርት የሚሰጥባቸው ት/ቤቶች ሥራ ሊጀምሩ ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል። እነማን እንደሚማሩበትና መግቢያ መስፈርቱ ምን እንደሆነ የምንደርስበትን ወደፊት የምንገልፀው ይሆናል።

5.7. **የውጪ ሀገር ከፍተኛ ትምህርት፡-** ውጪ ሀገር ሄዶ መማርን እንደትልቅ እድል ለሚቆጥሩ ተማሪዎች ይህ የመውጪያ በር እንደስኬት የሚወሰድ ሲሆን በጽንፈኝነት ለመማፋት የወሰኑ ተማሪዎች እድሉ ተመቻችቶላቸዋል፤ በሌላ በኩል ከክርስትና ወደእስልምና የተቀላቀሉ የቲዎሎጂ ተማሪዎች በፍጥነት የውጭ ሀገር ትምህርት እድል ተመቻችቶ ወደውጪ ይላካሉ። ብዙዎች በህግና በፖለቲካል ሳይንስ እንዲሰለጥኑ ይበረታታሉ። በዚህ ዓይነት ከሚላኩት ውስጥ ገሚሶቹ የሃይማኖቱን ትምህርት ተምረው የወሃቢያን አስተሳሰብ በትውልዱ ውስጥ የሚያሰረፁ ሲሆን ቀሪዎቹ ደግሞ በአካዳሚክስ ትምህርት ሰልጥነው ሲመለሱ ከፍተኛ የስልጣን ወንበር ስለሚያገኙ ለእስልምና ድርሻቸውንየሚያበረክቱበት ስልት ሥራ ላይ ውሏል። ባለፉት አመታት ቁጥራቸው ከ17 ሺህ በላይ የሚሆኑ ወጣቶች ተልከው በመማር ላይ ይገኛሉ። ክርስቲያኑ ግን ውጪ ተምሮ ወደሀገሩ የመመለስ ሀሳብ የሌለው ሲሆን የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ተምረው መጥተው እንዲያገለግሉ ሲላኩ በዚያው የሚቀሩና ቀሪውን የህይወት ዘመናቸውን ኑሮ ለማደላደል የሚሠሩ መሆኑ ሲታሰብ ምን ይሻላል ያሰኛል።

6 የአረቢኛ ቋንቋ ትምህርት የማስፋፋት ስልት

ዐረቢኛ ቋንቋን ለማስፋፋት ከሚፈልጉባቸው ምክንያቶች አንዱ ልዩ ልዩ ቋንቋ ተናጋሪ የሆነውን ኢትዮጵያዊ ሙስሊም በአንድ መንፈስ በዐረቢኛ ቋንቋና ባህል ሥር ለማደራጀትና አንድ ቋንቋ ተናጋሪ ለማድረግ ታስቦ ነው። ኢትዮጵያዊ ሙስሊሙን ከኢትዮጵያዊ ማንነቱ አውጥቶ ዐረባዊ ማንነት ያለው ሙስሊም ፈጥረው ባህሉና አለባበሱ ልማድና ወጉ ሁሉ ፍፁም ዐረባዊና ጽንፈኛ ሆኖ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ የመለየት የረጂም አመት

ሥራ ነው እየተሠራ ያለው። ይህ የአረባዊነት ፕሮጀክት በአንዳንድ አካባቢዎችና ብሔረ-ሰቦች ላይ ጎልቶ ይታያል። የመከባበርና የመቻቻል ባህላችን ዋጋ እንዳይሰጠው ተደርጎ በኢትዮጵያ ውስጥ መቻቻል እንዳልነበረ እና፤ በአንባሩ አስላሞች ሌላውን የኢትዮጵያ ህዝብ እንደቻሉት በማስረዳት ተቃራኒ አመለካከት እንዲይዝ ያደርጉታል።

አሁን ግን ጊዜው እንደተለወጠ ያስተምሯቸዋል። ለዚህ ነው ያልተለመደውን የዐረቢኛ ቋንቋ ት/ቤቶች በብዛት የምናየው ለዚህ ነው ኢትዮጵያዊ ያልሆነ የሴቶችና የወንዶች አለባበስ ዘውትር የምናየው። ይህም ድርጊት በአወሊያ ትምህርት ቤት ውስጥ ለ40 አመታት ያህል ከተሰራ በኃላ መንግስት አረቢኛ ትምህርት ክፍል ላይ ባደረገው ጥናትና ከዚያ ትምህርት ቤት ወጥተው በተለያዩ የኢትዮጵያ ከተሞች ላይ አምነትን መሰረት ያደረገ ስደትና የትምህርቱ ግንኙነት እንደነበረው ጥናት የተደረገ ሲሆን ትምህርት ቤቱ በቋንቋ ምህራን ስምና የትምህርቱ ይዘት ተጠንቶ የሃገሪቱ ህግ በሚፈቅደው መሰረት በከፍተኛ ትምህርት ተቁዋም ስር እንዲሆን ተደርጎአል ። የትምህርት ካሪኩለሙም በመንግስት የሚቃኝ መሆኑን መረዳት የአረቢኛ ትምህርት መምህራን ከቋንቋ ጥናት ጋር የውሃቢያን ፍልስፍና አስርገው የማስገባት አዝማሚያን ለመግታት የተደረጉት አካሄዶች የአወሊያ ትምህርት ቤት የአመጹ መነሻ ምክንያት ሆኖአል

7 ቤተ ክርስቲያንን የመርገም ስልት

ከፍተኛ የመርገም ችሎታ ያላቸውን ሰዎች በሀገሪቱ ሁሉ ላይ አሰማርተው ያስረግማሉ። በየማለዳውና በየሰዓቱ የጸሎት ጊዜ የእርግማን ቃል በቤተ ክርስቲያን ላይ ይናገራሉ። እርግማኑ ይሥራም አይሥራም እነሱ ግን ከተግባሮቻው እንደ አንዱ አድርገው እየተጠቀሙ ይገኛሉ። ይህንን የእርግማን ቃል ግን ሰይጣን ወደ

ፍጻሜ ለማምጣት መሞከሩ አይቀርም ይሁንና እግዚአብሔርን በመታመንና በቁሞሚነት በሚታዘዙ ዘወትር አይናቸውን በስራቸው ላይ በሚያሳርፉ የእግዚአብሔርን እርዳታ በሚጠሩት ላይ አይሰራም እንጂ ፊጽሞ ወላፈኑ አያገኘንም ማለት ላይሆን ይችላል። ሰይጣንና ስራውን ዝቅ አድርጎ መገመት ሌላው የሰይጣን መሳሪያ እንዳይሆንም ይሰጋል አንድ ሰው ለፈጣጋትም የሁን ለቁምነገር እንዳለው ምናልባት አትም ያሳጣን ይህ ሚርት ይሆን እንዴ? በርግጥ የጸሎት ጉልበት ማጣትና ክርስቶስን የመስበክ አትም ማነስ ዘወትር ከሚደረጉት እርግማኖች ጋር ግንኙነት በኖራቸውስ?

8. የጎሳ መሪዎችን አስቀድሞ በመያዝ ተከታዮችን የማስለም ስልት

ይህ ስልት በብዙ የአፍሪካ ሀገሮች የሚሠራበት ስልት ነው። በመጀመሪያ የአንድን ጎሳ መሪ ወይም ተደማጭ ሰው በመፈለግና እሱን የማስለም ሥራ ይሰራል። እሱ ከሰለመ የዚያ ጎሳ አባሎች በሙሉ እንዲሰልሙ ይደረጋል። ይህም የሚከናወነው በአብዛኛው የጎሳ መሪውን በሚያስፈልገው ሁሉ በመርዳት ወይም የኢኮኖሚ ችግሩን እንዲወጣ በማድረግ ነው። በኢትዮጵያ የኦሮሞን ብሔረሰብ በስፋት እንዲሰልም ከተደረገባቸው በርካታ መንገዶች አንዱ ይህ ስልት ሲሆን በአንድ መሪ ላይ በመሥራት ብዙ ተከታይ የማፍራት ውጤታማ ስልት ነው። ቤተክርስቲያንም ይህንን ስልት የወንጌል ስርጭት አካል ብታደርገው ይጠቅማታል።

9. መጽሐፍ ቅዱስን በተሳሳተ መንገድ ሙስሊሞችን የማስጠናት ስልት

ይህ ስልት ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን በማጣመምና እርስ በእርሱ የሚጋጭ መፅሐፍ እንደሆነ አድርጎ በማቅረብ የማስጠናት ዘዴ ሲሆን በዚህም ተከታዮቻቸው የእስልምና ሃይማኖት ትክክለኛው

ሃይማኖት እንደሆነ አባሎቻቸውን የሚያስተምሩበትና ክርስትና የተሳሳተ እምነት እንደሆነ የሚሰብኩበት አሠራር ነው። በተለይ በአሁኑ ወቅት አንዳንድ የሙስሊም እምነት ተከታዮች የክርስትና እምነት እርስ በእርሱ እንደሚጋጭ የተሳሳተ እምነት እንደምንከተል በድፍረት እስከመናገር ድረስ ደርሰዋል። ይህ ጉዳይ አደገኛ እየሆነ የሚሄደው በአንዳንድ አካባቢዎች በስህተት እንደምንመራ መገንዘባቸው ሳይሆን ወደትክክለኛው መንገድ ለመምራት ሃይል የሚፈቅድ አካሄድ በማመናቸው በመጽሃፎቻችን ላይ የጀመሩት ዘለፋ የት ጋ እንደሚቆም ድንበሩ አይታወቅምና ቤተክርስቲያን ቆም ብላ ማሰብ ይኖርባታል።

10. ገጠሩን ትኩረት አድርጎ መንቀሳቀስ

ብዙ ያልተማረ ህዝብ የሚበዛበትን የገጠሩንና የገጠር ከተሞችን አስላም ለማድረግ ምንም ተከታይ በሌለባቸው ቦታዎች ሳይቀር መስጊድ መገንባትና አንድ ቤተሰብ መድቦ እዚያው በማስቀመጥ አካባቢውን የሚያስልሙበት አሠራር ነው። በአንዳንድ አካባቢዎች በተለይም ባህላዊ እምነት በሚከተሉ ህዝቦች አካባቢ ይህ ስልት ሲሠራበት ማየት ይቻላል።

11. የንግድ ቦታዎችን በማለሰብ ስም መመራትና በሰዓ በመግዛት ለመስጊድ መሥሪያነት ማዋል

በተለይ እንደ አዲስ አበባና ሌሎች ትላልቅ የሀገሪቱ ከተሞች የእምነት ህንፃዎችን በቀላሉ መገንባት በማይቻልባቸው ቦታዎች በዚህ ዘዴ ይጠቀማሉ።

12. ለዘብተኛውንና ባህላዊውን እስላም አክራሪ የሚያደረግ ስልት

ከ1983 ዓ.ም በፊት የነበረው የኢትዮጵያ ሙስሊም አብዛኛው ባህላዊ ሙስሊም ሲሆን ቀሪው ደግሞ ለዘብተኛ ነበር። ከ1983 ዓ.ም ወዲህ ግን ወሃቢያ በይፋ መንቀሳቀስ ሲጀምር ይህን የአክራሪነት አስተሳሰብ ለማስረፅ የተጠቀመው ስልት ለዘብተኛውንና ባህላዊውን ሙስሊሙ አክራሪ ማድረግና ለቁርአናዊ ተልእኮ ማዘጋጀት ነው። (ሱረቱ አል አንፋ 8:39)

ቁረዐናዊ ተልዕኮ ተብሎ በሱረቱ አንፋል 8:39 ላይ የተጠቀሰው ቃል "ዕውከትም እስከማትገኝ ሐይማኖትም ሁሉ ለአላህ ብቻ እስከሚሆን ድረስ ተጋደሉአቸው ቢከለክሉም አላህ የሚሠሩትን ሁሉ ተመልካች ነው"ይላል በሌላ አነጋገር ጀሀድ አውጁባቸው ማለት ይመስላል። ክርስትናን ከምዕራባውያን ቅኝ ገዥዎች ጋር በማገናኘትና የሐሰት ፕሮፖጋንዳ በመንዛት ማስጠላት ዋና ተግባሩ ነው። ክርስትናንና መስቀልን እንዲጠሉ ይደረጋሉ። ለምሳሌ፦ በመዲና ክተማ አውሮፕላን ማረፍም ሆነ በአየር ክልሉ ማለፍ አይፈቀድለትም ምክንያቱም የመስቀል ቅርጽ አለው ብለው ስለሚያምኑ ነው።

ለ. ፕሮፓጋንዳዊና ፖለቲካዊ መልኮች

13. ታሪክን የማዘባት ስልት (ታሪክን ማስለም)

እስልምና የኢትዮጵያን ምድር ከረገጠበት ጊዜ ጀምሮ ስለኢትዮጵያ እስላማዊት ሀገር መሆን ዐረባዊ የፈጠራ ታሪክ ሲጽፉና ሲያስነግሩ የቆዩ ሲሆን ታሪክን አዛብቶ በማቅረብ ዓለም በተለይም የባህረ ሰላጤው ሀገሮችን ይሁንታ ለማግኘት ያልተደረገ ሙከራ ያልተጻፈ መጽሐፍ የለም። በኢትዮጵያ የእስልምና ታሪካዊ አመጣጥ ለመግለጽ እንደተሞከረው በ620 ዓ.ም መሐመድ እስልምናን

እንዲቀበሉ የማስፈራሪያ ዛቻ ከጻፉላቸው ሀያላን መንግስታት መካከል እስከ የመን ድረስ ያስተዳድር የነበረው ሃያሉ የአክሱም ንጉስ አድርያዝ (የኢትዮጵያው ንጉስ) ፈርቶ እስልምናን ተቀብሏል። በዚህ ምክንያት "ኢትዮጵያ የእስላም ሀገር ናት" ይላሉ ፡ የእስላም ሀገር ከነበረች መቼና እንዴት ክርስቲያን እንደሆነች አይጽፉም አይናገሩምም። ያ እስልምናን የተቀበለው ንጉስ "ነጃሽ" ይባል ነበር በማለት በዚህ ስም ዙሪያ ተንጠላጥለዋል። ንጉሱ ነጂሽ ከነበረ እሱ ከሞተ በኋላ አልጋ ወራሹ ማን ነበር? ለምን ከዚያ በኋላ ያሉት ነገስታት በሙሉ ሙስሊሞች እንደነበሩ በቀጣይ ታሪኮች አልተመዘገበም? የፈጠራው ታሪክ ዋናው ማጠንጠኛ ይህ ስም ስለሆነ ዛሬ በሀገራችን ለት/ቤቱ፣ ለማተሚያ ቤት፣ ለመስጊድና ለቀብር ቦታ ወዘተ ስሙን በመስጠት ለማጽናት እየሞከሩ ይገኛሉ። በሀገር ውስጥ የሚታተመው ቢላል የተሰኘው መጽሔት የነጂሽን የእስልምናን እምነት መቀበልን ጨምሮ ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ እስላማዊት ሀገር እንደነበረች በተደጋጋሚ ጽፎ አስነብቧል ዛሬ ሙስሊሞችን ከሚያስቆጣቸው ነገሮች ሦስቱ

1. ኢትዮጵያ የክርስትያን ደሴት ናት
2. ክሩሴድ
3. ነጂሽ አልሰለመም የሚሉት ናቸው።

የሌሰ ታሪክ የመጻፍ አሊያም ያለን ታሪክ እውነት የማዛባት ስራ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲሰጣቸሁ አል ዓለም አል አል ኢስላም ጋዜጣ ሃምሌ 20 ቀን 1990 ዓ.ም ባወጣው እትም የሚከተለውን ጽፎአል

- ኦሮሞዎች ብዙ ቁጥር ካላቸው የኢትዮጵያ ህዝብ መካከል ሲሆን ቁጥራቸው ሃያ ሚሊዮን ይደርሳል።
- ኦሮሞዎች ከጥንት ዘመን ጀምሮ ከአረቦች ጋር ግንኙነት አላቸው
- እስልምና ወደ አፍሪካ ከመግባቱ በፊት በነቢዩ ዘመን ሙስሊም ስደተኞችን ተቀብለው ካስተናገዱት

የመጀመሪያዎቹ የምስራቅ አፍሪካ ህዝቦች መካከል አሮሞዎች ይገኛሉ

- ቁርአንን በመከተል የመጀመሪያዎቹ አፍሪካውያን አሮሞዎች ናቸው
- ስደተኞች ከተመለሱ በኋላ እስልምናን በአፍሪካ የማስፋፋቱን ተግባር ተረክበው የተገበሩት አሮሞዎች ናቸው
- አሮሞዎች እስልምናን የተቀበሉት በ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው
- አሮሞዎች ራሳቸው ራሳቸውን እንደአረቦች ነው የሚቆጥሩት
- የጥንት ዝርያዎቻቸው ከአረብ ልሳነ ምድር እንደመጡ ትውልዳቸውም ከሁለት የየመን ነገዶች ከአል አገታድ እና ከአል ዘፋድያ ነው ይላሉ እንግዲህ የሙስሊም ሊግ ልሳን የሆነው ጋዜጣ እነዚህን የመሳሰሉ የፈጠራ ታሪኮችን በየወቅቱ እየጻፉ በሚያሰራጩት ታሪክ የማዛባቱን ስራ ገፍተውበታል።

ከዚህ እምነት በመነሳት በዓለም ሙስሊም ሊግ ከፍተኛ አመራር ውሳኔ መሰረት የኢትዮጵያን መንግስታዊ አሰተዳደር እስላማዊ አገዛዝ በማድረግ «<u>የነጃሺን አገር ወደ ቀደመ እስላማዊነት መመለስ</u>» አለብን ብለው በከፍተኛ ደረጃ እየሰሩ ይገኛሉ። በየካቲት ወር 2004 ዓ.ም የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስተርና በብሮድካስት ባለስልጣን ትብብር ለመገናኛ ቡዙኃንና ለሕዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች በተዘጋጀ ስልጠና ላይ በቀረበ የጥናት ወረቀት ጥናት አቅራቢዋ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትር ከፍተኛ ባለስልጣን ከጠቀሰዋቸው አራት ዋና ዋና ነጥቦች አንዱ የወሀቢያ ዓላማ በረጅም ጊዜ ዕቅዱ እስላማዊ መንግስት መመስረት እንደሆነ የደረሱበት መሆኑን ሀላፊዋ አረጋግጠዋል ሲል

የሙሲሊሞች ጉዳይ ቅጽ 2 ቁጥር17 የካቲት 2004 ዓ.ም የተሰኘ የእስላም መጽሔት አባባሉን ተቃውሞ ጽፏል።የፈጠራውን ታሪክ እውን ለማድረግ ምን ያህል ተግተው እንደሚሰሩ ክርስቲያኖች ትምህርት ሊሆነን ይገባል። የታሪክ ማዛባቱ ዋና ዓላማና ግብ በነሱ አባባል «<u>ሀገራቱን ወደ ቀደመ እስልምና መመለስና እስላማዊ መንግስት መመስረት</u>» በመሆኑ ጥር 2004 ዓ.ም ተጀምሮ በየካቲት ወር 2004 ዓ.ም እንዲያበቃ የተደረገው የአወሊያ ኮለጅ ንቅናቄ ዓላማ ተመሳሳይ እንደሆነ መጋቢት 10 2004 ዓ.ም የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ጋዜጣዊ መግለጫም በግልጽ አስቀምጧል። ታሪክ የማዛባቱ (የማስለመሙ) ተግባር ከውጭ የዐረብ ፀሃፊዎች ጋር እየተቀባበሉ በተጠናከረ ሁኔታ በማስኬድ ላይ መሆናቸውን ለማመልከት የውጭ ጸፊዎች ያሏቸውን እስቲ እንመልከት፡-

- በሶሪያ አገር ቀላይ አምራ በሚገኘው የአወሊድ ቤተ መንግስት ውስጥ በተሳለው ስዕል ለእስልምናው የገበሩ መንግስታት ምስል ዝርዝር ውስጥ የአክሱሙ ንጉስ ይገኝበታል። ነገር ግን በአርኪዮሎጂ ቁፋሮ በተገኘ መረጃ መሰረት የዚያን ዘመን ንጉስ ይጠቀምበት የነበረው ሳንቲም..ገንዘብ.. ላይ የመስቀል ምስል እንደነበረበት ታሪክ ዘግቧል።
- በ1980ዎቹ በካይሮ ይታተሙ የነበሩ የአክራሪ ሙሲሊሞች ስነጹሑፎች ..ኢትዮጵያ ጥንትም ሆነ ዛሬም የካፊሮች የከሀዲዎች አገር የአክራሪ መስቀል ጦረኞች እስልምናን መሐመድን የጠላች የምትጠላ አገር ነች ይላል ብለው ይጽፉ ነበር።
- «ወደ ኢትዮጵያ የተደረገው ስደትና የነጃሺን እስልምና አስመልክቶ የተነሳ ውዝግብ» በተሰኘ መጽሐፍ ሲጽፍ የነጃሺን ወደ እስልምና መለወጥ መቃወም ወይም መጠራጠር ጸረ-እስልምና ነው ይላል።
- ይሄው ጸሐፊ ሲጽፍ ..ኢትዮጵያ እስልምናን የተቀበለ ንጉሥዋን በመቃወም እርሱ ከሞተ በኃላ መሐመድ ለንጉሱ የጻፉትን በማጥፋት አገሪቱ ጸረ-እስልምና አቋሟን አሳይታለች ይላል።
- በጣሊያን ወራራ ወቅት የወሃቢያ ዋና አቀንቃኝ የነበሩት የሳዑድ ዐረቢያው ንጉስ የሚከተለውን ተናግረው ነበር

«ኢትዮጵያ እስልምና የተሸነፈባት ክፉ ሰይጣናዊ ሀገር ናት» ብለው ነበር።

- ሐምዛ የተባለ ጸሐፊ «<u>የዐረብ ልሳነ ምድር ልብ</u>» በተሰኘ መጽሐፉ ኢትዮጵያዊያን ይገዙ በነበረበት ዘመን ካዓባን ሊያፈርሱ አስበው ነበር ብሎ ጽፏል።
- ሌላው የሶሪያ ታዋቂ ጸሐፊ «<u>የኢትዮጵያ ሙስሊሞች</u>» በሚለው ጹሑፉ ለክርስትና ያለውን ጥላቻ ከመግለጹም በላይ ..እስልምና በኢትዮጵያ እንደገና እንዲያንሰራራ የሞሰሊኒ ወራራ መደገፍ አለበት ብሏል። ይሄው ጸሐፊ አያይዞ ሲጽፍ ኢትዮጵያ ለጅማና ለሐረር የራስ ገዝ አስተዳደር ካለሰጠች ውድመት ይጠብቃታል ብሎ ያስጠንቅቅና አስፔን ሙሲሊሞች በሰተቀር በዓለም ላይ እንደ ኢትዮጵያ ሙሲሊሞች ብዙ መቶ ዓመታት መከራ የተቀበለ ማንም የለም ብሏል።
- ዚያድ ባሪ ከ1969 ዓ.ም የለኮሰው ጦርነት በኢትዮጵያ አሸናፊነት ሲጠናቀቅ የሪያድ ሬዲዮ ጣቢያ የሚከተለውን መልዕክት ያስተላልፍ ነበር ..አጋዴንና ኤርትራ ከጥንቱ የዐረብ ሙሲሊም ሕዝቦች ናቸው።በኢትዮጵያ የተከፈተው ጦርነት የነጻነት ጦርነት ነው። ኢትዮጵያን ለማስለም ባለቸው የቆየ ቁርጠኛ አቋም ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ክርስትና ለማፍረስ የሚፈጽሟቸው ድርጊቶች በሙሉ የነጻነት ጦርነት ነው ብለው ይቆጥራሉ።
- በንጉስ ሳዑድ ዩኒቨርሲቲ በስነ ትምህርት ዘርፍ የእስልምና ጥናት ዲፓርትመንት ባልደረባ የሆነው ዓሊ አሊሸኪ አሕመድ በክር <u>"ወደ ኢትዮጵያ የተደረጉ የሁለቱ ..ሂጅራዎች መለያ ባሕሪያት"</u> በተሰኘው የባለ 258 ገጽ መጽሐፍ ሶስት አሳቦችን አስፍሯል፦

ሀ. ነጃሺ እስልምናን በመቀበሉ ምክንያት ኢትዮጵያ ሁል ጊዜም የእስላም ሀገር ልትሆን ችላለች ይላል

ሰ. ነጃሺ እስልምናን በመቀበሉ ምክንያት እስልምና በኢትዮጵያ ያገኘው ድል አለቀጠለም። ይህም ማለት ሳሀባዎች..የመጀመሪያዎቹ የእምነቱ ተከታይ ስደቶች..

ወደ ሀገራቸው ከተመለሱና ነጃሺ ከሞተ በኃላ ኢትዮጵያ ሙሉ ለሙሉ ሰለ መስለሟ የታሪክ ማስረጃ አለመኖሩን ይገልጽና ለኢትዮጵያ የተሰጠውን ትኩረት አነስተኛነት ያነሳል። በዚህ ወቅት ግን እስልምና የዐረቡን ልሳነ ምድር ማጥለቅለቁንና ኢትዮጵያ ግን የዚህ ዕድል ተጣቃሚ መሆን አልቻለችም በማለት ኢትዮጵያ የእስላም ሀገር ያልነበረች መሆኗን ይመስክራል።

ሐ. ጨቋኙ ክርስትና እስልምናን በኢትዮጵያ አዋርዶአል ወይም በሌላ አነጋገር ጨቋኙ በክርስትና ሐይማኖት ምክንት አስልምና በኢትዮጵያ ሊዋረድ ችሏል ሲል ያትታል።

- በ1993 ዓ.ም የወጣው የባክር መጽሐፍ ያነሳቸውን ነጥቦች በጠነከረ መንገድ የገለጸው ደግሞ መሐመድ አልታዩብ ቢን የሱፍ የተጻፈ ባለ 700 ገጽ መጽሐፍ <u>"ኢትዮጵያ ዓረባዊነትና እስልምና በታሪክ ውስጥ"</u> በተሰኘ ርዕስ የሚከተሉትን አሳቦች አስፍሯል

ሀ. ኢትዮጵያ እስላማዊት ሀገር ናት ይልና ለዚህም ምክንያት አድርጎ የሚያቀርበው ከሀገሪቱ ሕዝብ 80 በመቶ ሙሲሊም ነው ብለው የሚጽፉ ጸሐፊዎችን መነሻ ያድረጋል። ለምሳሌ አቡ አህመድ ኢል ኢትዮብ የተባለው ጸሐፊ "የቆሰለው የኢትዮጵያ እስልምና" በተሰኘ መጽሐፉ ወደ 75 በመቶ እንደሚደርስ ይናገራል።

ለ. ኢትዮጵያዊያን ሙሲሊሞች ዐረቦች ናቸው ካለ በኋላ የኢትዮጵያውያንን "የጠራ ዐረብነት" ሲጽፍ ይህን የማይቀበሉ ሰዎችንም የምስረቅ አፍሪካና የዐባይ ሸለቆ ሕዝብና የዐረብን ሕዝብ ታሪክ ነጣጥለው የሚያዩ ኢምፔሪያሊስቶች ናቸው ሲል ይገልጻል።

ሐ. የአማራ ክርስትና በዓለም ደረጃ እስልምና ላይ የተጠነሰሰ ሴራ ነው ይልና ይህኑኑ ሲያብራራ የእስልምናን ታጋሽነት ጠቅሶ የክርስትናና የአይሁድ ሀይማኖቶች ግን እስልምና ላይ ደባ ከመስራት ወደኃላ እንደማይሉ ያትታል።ሌሎች ብዙ ጉዳዮችን አንስቶ ይዘረዝራል

መ. አህመድ ግራኝ ያወጀው ጀሃድ የእስለምና ሀይማኖት ጠላቶችን መቋቋሚያ ትክክለኛ መንገድ ነው ብሎ ሲያብራራ እንዲህ ይላል"የእስልምና ጠላቶች ከጊዜ ጋር እየተሸቀዳደሙ በኢትዮጵያ ያለውን የእስልምና ሀይማኖት ለማውደም ተከታዮቹን ክርሲቲያን ለማድረግ በሚጥሩበትበአሁኑ ወቅት የዐረብ መንግስታትና ድርጅቶች ለመርዳት መነሳት አለባቸው። ይህ ዕርዳታ ሲደርሳቸው ሙሲሊሞች በዕምነት ጠንከረው የመስቀል ጦረኞችን ይቃወማሉ ከዚህ ውጭ ይህን ድርጊት ለማከነወን ችል ማለት እስልምናን አደጋ ላይ ይጥለዋል ስለዚህ ሙስሊሞች ነቀተው እንዲነሱና የሚመጣውን አደጋ ተቋቋመው እስልምናን ከወንጌል ሰባኪዎች እንዲታደጉ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ" ይላል

ሠ. በኢትዮጵያ እስልምና ተሃድሶ ሊደረግበት ይገባዋል ይህ ሲደረግ ግን መሆን ያለበት በሚሲጥር ነው ይልና መፍትሔውም ሲጠቀም የሚከተለውን ብሏል "የሀገሬውን የዕምነት አስተማሪዎች በድጋሚ ማሰልጠንና ማስተማር ምክንያቱም ታዋቂ የተባሉት ሊቃውንት እንኳን ቢሆኑ በዘመናዊ ትምህርት የሰለጠኑ ባለመሆናቸው የዕውቀት ደረጃቸውን ከፍ ለማድረግ ተማሪዎችን በተገቢውና በዘመናዊ መንገድ ማስልጠን ከሚመጣባቸው ፈተና እንዲቋቋሙ ማድረግ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ መድረሳዎች ጠላት ሊያይና ሊነቃ በማይችልበት መንገድ በሚስጥር መርዳት ይህንንም ለማድረግ ማጎበረስቡን ከሚያስተዳድሩ የየአካባቢው የእምነቱ መሪዎች ጋር መተባበር እንግዲህ ታሪክን የማዛበቱ ጥንስስ የተጀመረው ዛሬ ላይሆን ድሮ መሆኑንና ዐረቦች በመጻሐፎቻቸው የአገር ውስጡንና የውጭውን የእስልምና ሀይል ለመነሳሳት የተጠቀሙባቸውን የመቀስቀሻ ጽሑፎችን ተመልክተናል ከእነዚህ ጹፎች የምንገነዘባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች:-

